የወንጀል የፍትህ ሥርአት ማሻሻያ ግብ በአሰራር ላይ የሚታዩ ክፍተቶች ችግሮቻና የመፍትሄ አቅጣጫዎች

በፍትህ አካላት ባለሞያዎች ስልጠና ሞዴል ለ3ኛ ዙር ቅድመ ስራ ስልጠና ፕሮግራም ሰልጣኞች የቀረበ፡፡

አቶ አሊ መሀመድ አሊ
መጋቢት 2000 ዓ/ም
አዲስ አበባ

መግቢያ፡ -

የወንጀል የፍትህ ሥርዓት (Criminal Justice System) የሚለውን ፅንስ ሀሳብ በተለያየ መልክ የተሰሙ መፁራን የተለያየ ትርጓሜ የሰጡት ቢሆንም በዚህ ፅሑፍ " Criminal justice is the sum total of society activities to defend it self against the action it defines as criminal የሚለውን ትርጉም ተጠቅሜለሁ፡፡ ከዚህ ትርጓሜ እንደምንረዳው የአንዲት አገር የወንጀል የፍትህ ሥርዓት የአንዲት አገር ህዝብ ራሱን ከወንጀል ድርጊት ለመከላከል የሚፈፅማቸው ሁለገብ ተግባራት በአጭሩ ለመግለፅ የሚያገለግል ፅንሰሀሳብ ነው፡፡ ይህንን ትርጓሜ መሰረት በማድረግ ሲተነተን የአንዲት አገር የወንጀል የፍትህ ሥርዓት፣

- የአገሪቱን የወንጀል ህግና የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ እና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው የህግ ማዕቀፎች ፣
- ወንጀልን ለመከላከል የተነደፉ ስትራቴጅዎች፣
- የወንጀል መከላከል ተግባር የሚፈፅሙ የተለያዩ አደረጃጀቶችና ፖሊስና ሌሎች የፀጥታ አስከባሪ አካላት፣
- የአገሪቱን የወንጀል ህግ በመጣስ የወንጀል ድርጊት የሚፈፅሙ ሰዎችን ለፍርድ ለማቅረብና ለማስቀጣት እንዲሁም የተወሰነውን የወንጀል ቅጣት ለማስፈፀም የተቋቋሙ የፍትህ አካላት ማለትም ፖሊስ ዐቃቤህግ፣ ፍርድ ቤቶች፣ ማረሚያ ቤቶችና ሌሎች ተመሣሣይ ተግባርና ሀላፊነት ያላቸው አካላት ለምሳሌ የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽኖች፣
- ስለ ወንጀል አይነቶችና የወንጀል አፈፃፀም ስልቶች እና መንስኤዎች እና ወንጀሎቹን ለመከላከል ስለሚያስፈልጉ ስልቶች በማጥናት የመፍትሔ ሀሳብ የሚጠቁሙ የወንጀል የመረጃ ማዕከሎች እና ሌሎች የጥናትና የምርምር ተቋማት እና በአጠቃላይ በመንግስትና በህብረተሰቡ ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚደረጉ ሁለገብ እንቅስቃሴዎችን ሁሉ አካትቶ የሚይዝ ፅንሰ ሀሳብ ነው፡፡

የማንኛውም አገር የወንጀል የፍትህ ሥርዓት የህግ ማዕቀፎችን በማወጅ እና ህጉን ለማስፈፀም የሚቹሉ የተለያየ የሥራ ተግባርና ድርሻ ያላቸው ተቋማት በማቋቋምና የተቋማቱ የማስፈፀም አቅም በማጎባት መንግስትንና የህዝቡን ሠላምና ደህንነት በማረጋገጥ ጥረት ያደርጋል የወንጀል የፍትህ ሥርዓትም ከላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት በአግባቡ በማከናወን የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የህግ የበላይነትና ልዕልና የሰፈነበት አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብና አንድ የኢኮኖሚ

ማህበረሰብ ለመገንባት ያስቀጣሉትን ሕገ መንግስታዊ ግብ እንዲሳካ ለማድረግ የበኩሉን አስተዋፅኦ ማበርከት ይጠበቅበታል፡፡

ይኸንን የወንጀል የፍትህ ሥርዓት መሠረታዊ ግብ ህግ አውጪው በኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 1 በመጀመሪያው ፖራግራፍ " የወንጀል ህግ አላማ በጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን፣ የመንግስትን የሕዝቦቹንና የኗሪዎችን ሰላምና ደህንነት ሥርዓትና መበትና ጥቅም ማጠበቅና ማረጋገጥ ነው " በማለት በግልፅ ደንግጎታል፡፡ እዚህ ላይ የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ መሠረታዊ ዓላማና ግብ ግልፅና የማያሻማ መሆኑ ብዙ መወያየት የማያስፈልገው ነጥብ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ገና ሰፊ ሥራ የሚጠይቁ በርካታ ጉዳዬች እንዳሉ፣ በዚህ ሴሚናር መሳተፍና መታየት አለበት፡፡ ከነዚህም ጥቂቶቹ

- የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ ይህንን ግብ ለማሳካት የሚችለው እንዴት ነው?
- የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ ይህንን መሠረታዊ ግብ እንዳያሳካ እንቅፋት የሆኑ የአደረጃጀት የህግ አተረጓጎምና የአፈፃፀም ችግሮች ምንድን ናቸው?
- የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ የተጣለበትን ከባድ ሀላፊነት ለመወጣት ወደፊት በትኩረት ሊታዩ ግልፅ ወይይት ሊደረግባቸውና ሊሻሻሉ የሚገቡ ጉዳዬች ምንድን ናቸው?
- ችግሮቹን ለመቅረፍ በሚደረገው ጥረት ውስጥ ወንጀልን ከመፈፀም በፊት የመከላከልና ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ ወንጀልን የመመርመርና የመቆጣጠር ሀላፊነት ያለባቸው አካላት ምን ይጠበቃል የሚሉትና ሌሎች ነጥቦች ጥልቅ ጥናት፣ ወይይት በሚደረግና መሟላት የሚገባቸው የአደረጃጀት የአሠራርና ሌሎች የህግ ማዕቀፎች በማሟላት የወንጀል የፍትህ ሥርዓታችን ካለፈው ሚሊኒየም የነበሩበትን የቅልጥፍና፣ የውጤታማነት የሥነ ምግባርና የብቃት ችግሮች በመቅረፍና በሁለተናዊ መልኩ ወንጀልና የወንጀል ሥጋትን ለመቀነስና የህብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት ለማረጋገጥ የአሳሳካከት የአሠራርና የአደረጃጀት ተሀድሶ ማድረግ ይገባዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ይህ አጭር ፅሑፍ የአገራችን የወንጀል የፍትህ ሥርዓት ያሉበትን ዙሪያ መለስ ችግሮች ለማዘርዘርና የመፍትሔ ሀሳብ ለማቅረብ ታስቦ የተዘጋጀ አይደለም፡፡ ሆኖም የወንጀል የፍትህ ሥርዓታችን ወንጀል ከመፈፀሙ በፊት በሚያደርጋቸው የመከላከል ሥራዎችና ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ በሚፈፅሟቸው የወንጀል ምርመራ፣ የወንጀል ክስ አቀራረብ፣ የወንጀል መዳትና የፍርድ አሰጣጥ ሒደትና የወንጀል ፍርድ አፈፃፀም ላይ የሚታዩ አንድ አንድ ነጥቦችን ለሴሚናሩ ተሳታፊዎች በማቅረብ ተሳታፊዎቹ ግልፅ የሆነ ወይይት በማድረግ የመፍትሔ ሀሳብ የሚፈለጉን እርምጃ እንዲጀመሩ ማሳሳት ነው፡፡

ፅሑፉ አምስት ከፍሎች አሉት፡፡ በመጀመሪያው የአገራችን የወንጀል የፍትህ ሥርዓት ወንጀል ከመፈፀሙ በፊት በመላላከል በኩል ያሉት ጠንካራና ደካማ ጎኖች ወንጀልን ከመፈፀሙ በፊት ዘላቂ በሆነ መንገድ መላላከል ወንጀልንና የወንጀል ሥጋትን ለመቀነስ በአገር እና በክልል ደረጃ መሠራት እና መሟላት ስላለባቸው ሁኔታዎች ለወይይት መነሻ የሚሆኑ ነጥቦችን በአጭሩ ለማቅረብ ሞክሬአለሁ፡፡ በሁለተኛው ምዕራፍ የወንጀል ምርመራ ሒደት፣ በሶስተኛው ምዕራፍ በወንጀል ክስ አቀራረብና መያት ሒደት በአራተኛው ምዕራፍ የወንጀል ፍርድና ቅጣትን በመወሰን ሒደት በአምስተኛው ምዕራፍ በወንጀል ፍርድና ቅጣትን በመከታተልና በማስፈፀም ሒደት በዚህ ሴሜፍር ተነስተው ወይይት ቢደረግባቸው ጠቀሜታ ይኖራቸዋል ብየ ያሰብኳቸውን ነጥቦች ላይ ትኩረት ሰጥቻለሁ፡፡ በመሆኑም በፁሁፉ የተነሠትን ሀሳቦች በማዳበር ተጨማሪ ነጥቦችን በማንሳትና የአጭር ጊዜና የረዝም ጊዜ የመፍትሔ ሀሳቦችን በሜላለግ የወይይቱ ተሣታፊዎች በላቀ ደረጃ በመሣተፍ፣ የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱን ካሉበት ችግሮች አላቅቆ ወጤታማና ቀልጣፉ ለማድረግ በችግሮቹና ችግሮቹ በሜፈቱባቸው ዘዴዎች ዙሪያ የጋራ መግባባት ላይ በመድረስ ለተግባራዊነታቸውም እንደሚረባረቡ ያለኝን ተስፋ ለመግለፅ እወደለሁ፡፡

ምዕራፍ አንድ

1.1 ስለ ወንጀል መላላከል

አንዲት አገር የህዝቡንና የኗሪዎቹን ሰላምና ደህንነት ለማረጋገጥ በግለሰብ ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች፣ የተደራጁ ቡድኖች ወይም በሌላ አገር መንግስት ወይም መንግስት መሳል ድርጅት የሚቃጣባትን ወንጀል እና ጥቃት ከመፈፀሙ በፊት መላላከልና ወንጀሉ ከተፈፀመም በኋላ ወንጀሉን የፈፀመው ክፍል ተጠያቂ እንዲሆንና ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኝ ቅጣቱም በአግባቡ እንዲፈፀም ሜድረግ ይጠበቅበታል፡፡ በሜናቸውም አገር የሜፈፀም የወንጀል መላላከል ተግባር በሁለት ምዕራፍ ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

- የመጀመሪያው ወንጀል ከመፈፀሙ በፊት መንግስትና ህብረተሰብ ራሱን ከወንጀል ለመላላከል የሜፈፀማቸው የወንጀል መላላከል ተግባራት Pro active crime prevention" ሲሆን፣ ሁለተኛው መንግስትና ማህበረሰቡ ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ የሜፈፀማቸው የወንጀል መላላከል ተግባራት (Re active Crime Prevention) ተግባራትን የሚያጠቃልል ነው፡፡
- ወንጀል ከመፈፀሙ በፊት የሚሠሩትን የወንጀል መላላከል ተግባራት አንድ አንድ ፀሐፊዎች የመጀመሪያ ደረጃ ወንጀል መላላከል (Primarily Crime

Prevention) እና ሁለተኛ ደረጃ "Secondary Crime Prevention" በማለት የሚከፍሏቸው ሲሆን ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ የሚሥሩትን ተግባራት ደግሞ Thirdly Crime Prevention" በማለት ይገልፁታል፡፡

- የመጀመሪያ ደረጃ የወንጀል መከላከል ተግባር የሚሉት በተለምዶ በአንድ ተቋም ወይም አካባቢ ወንጀል እንዳይፈፀም የሚደረገዉ የዕለት በዕለት የጥበቃ ተግባራት የሚያጠቃልል ነዉ፡፡ በመሆኑም በመንግስት ተቋማት በባንኮች፣ በነዳጅ ማደያ ዲፖዎች፣ በገበያ ማዕከላትና በመንገዶች ላይ የሚደረግ የዕለት በዕለት የጥበቃና የቅኝት ተግባር የመጀመሪያ ደረጃ የወንጀል መከላከል ተግባራት ናቸዉ፡፡ ስለዚህ የፖሊስ አካል፣ የሚሊሻ ሀይል ወይም ህብረተሰቡ በአንድ አካባቢ ወንጀል እንዳይፈፀም በመደበኛነት የሚያደርገዉ የጥበቃና የቅኝት /ፖትሮል/ ተግባር የመጀመሪያ ደረጃ ወንጀል መከላከል ተግባራት ወስጥ የሚመደቡ ናቸዉ፡፡ በአንድ አካባቢ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ብዛት የወንጀሎቹን አይነት የፈፃሚዎቹን ሁኔታ የወንጀል አፈፃፀም ስልት ላይ በመመሥረት እንዲሁም ወንጀል ለመሥራት የሚደረጉ ዝግጅቶችን የወንጀል ዕቅድና የወንጀል ሠሪዎቹን የግንኙነት መስመርና አደረጃጀት በማጥናትና በመተንተን ወንጀሎቹ እንዳይፈፀሙ በጥናት ላይ የተመሠረቱ ህጋዊ እርምጃዎችን በመዉሰድ ወንጀል ሴራዎችን ወንጀል ለመፈፀም የሚደረጉ ዝግጅቶች የወንጀል ተግባራት ከመሞከራቸው በፊት ለማምከን የሚሥራው የወንጀል መከላከል ተግባር ሁለተኛ ደረጃ የወንጀል መከላከል ተብሎ በሚፈረጀው የወንጀል መከላከል ዉስጥ የሚከቃለሉ ተግባራት ናቸዉ፡፡

ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ ወንጀል የፈፀመዉን ጥፋተኛ ለመለየት የተወሰደዉን ንብረት ለማስመለስ የሚደረገው የወንጀል ምርመራ አጥፊዉን በገለልተኛ እና ነፃ ፍርድ ሰጭ አካል ለማቀጣት የሚከናወነው የክስና የመሞት ሒደት ተከሳሽ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ በኋላ የሚወሰነው የቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃና በፍርድ ቤት የተወሰነዉን ቅጣትና የጥንቃቄ እርምጃ ለማስፈፀም አጥፊዎችን ለማረምና ጥሩ ዜጋ ለማድረግ የሚከናወኑ የፍርድ ማስፈፀም ተግባራት በአንድ በኩል ወንጀል የመፈፀም ህልምና ፍላጐት ላላቸው ሰዎች ተግባራዊ ማስጠንቀቂያ በማጠት ወንጀል የመፈፀም ሀሳባቸዉን እንዲተው በድረግ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ወንጀል ፈፃሚዎች ደግሞ ወንጀል የመፈፀም አቅም እንዲኖራቸው በማድረግና ተደጋጋሚ ወንጀለኝነትን በመቀነስና ወንጀልን በመከላከል ሒደት የበኩሉን አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡ ይሽም ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ በፍትህ አካላት የሚከናወነው ተግባር በአግባቡና ወጤታማ በሆነ መንገድ ከተከናወነ ወንጀልንና የወንጀል ስጋትን በመቀነስ በኩል የላቀ ድርሻ ያለው በመሆኑ እንደ ሶስተኛ ደረጃ የወንጀል መከላከል ተግባር ተደርጎ ይታያል፡፡

የወንጀል የፍትህ ሥርዓታችን የአገሪቱን የመንግስትን የህዝቦቹን የነዋሪዎቹን ሰላም፣ ደህንነት፣ ሥርዓት፣ መበትና ጥቅም ለማከበቅና ለሚረጋገጥ የሚሆለው በመጀመሪያ ወንጀል ከመፈፀሙ በፊት ውጤታማ የሆነ የወንጀል መከላከል ተግባራትን ለማከናወን ሲችልል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ ውጤታማና ቀልጣፉ በሆነ መንገድ የወንጀል ህጉን ተግባራዊነትና ተፈፃሚ ት ለማረጋገጥ የሚቻል ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ህግ አውጭው የወንጀል ህጉን የደነገገው በወንጀል ስለሚያስጠይቁ ድርጊቶችና ስለሚያስከትሉት ቅጣት ለአጠቃላዩ የማህበረሰቡ አባላት የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በማጠት ወንጀል ለመፈፀም ሀሳብና ፍላጎቱ ያላቸው ሰዎች ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡ በማድረግ የወንጀል ህጉ ወንጀልን ለመከላከል General Different effect " እንዲኖረው በማሰብ ሲሆን፣ የፍትህ አካላት በበኩላቸው የወንጀል ህጉን በመተላለፍ ወንጀል በሚፈፅሙት ላይ ደግሞ ህጉን በተግባር ተፈፃሚ በማድረግ አጥፊዎቹ ሌላ ወንጀል እንዳይፈፅሙ አቅም በማጣትና ለሌሎች በመቀጣጫ ት በማሰየት ማስተማሪያ እንዲሆኑና እንዲታረሙ ለማድረግ የወንጀል ህጉ ወንጀልን በመከላከል ረገድ " Specific Different effect" እንዲኖረው በማድረግ የወንጀል ድርጊትንና የወንጀል ስጋትን በመቀነስ የአገሪቱን የመንግስትን የሕዝቡንና የኗሪዎቿን ሰላምና ደህንነት በማረጋገጥ የወንጀል የፍትህ ሥርዓት ሠረታዊ ግብ ማሣካት ይጠበቅባቸዋል፡፡

እዚህ ላይ ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ የወንጀል ምርመራ ስናከናወን፣

- የወንጀል ክስ አቀራረብና የመጣት ሒደት፣
- በወንጀል ፍርድ አሰጣጥና የቅጣት ውሣኔ በምንወስንበት ጊዜ፣
- እንደዚሁም የወንጀል ፍርድና ቅጣቱን በምናስፈፅምበት ወቅት፣

ይኸ ተግባራችን ወንጀል የመፈፀም ሀሳብና ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች በማስጠንቀቅ ተደጋጋሚ ወንጀለኝነትን በመቀነስ በአጠቃላይ ወንጀል መሥራት ኪሣራ እንጅ ምንም አይነት ትርፍ የሚገኝ መሆኑና ወንጀል የሠሩ ሰዎች ደግሞ በፍትህ የሚያመልጠበት ክፍተት የሌለ መሆኑን በማረጋገጥ ወንጀልን በመከላከሉ ሒደት የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ የሚያበረክት መሆኑን በአግባቡ እየመረመርንና እየመዘን ነው? ወይስ ይህንን ግምትና ግንዛቤ ወስጥ ሣናስገባ የሚሰው መታየትና ወይይት ሊደረግበት የሚገባው ነጥብ ነው?

በአጠቃላይ የአንዲት አገር የወንጀል የፍትህ ሥርዓት የተቀመጠለትን መሠረታዊ ግብ ለማሣካት የሚቻለው ወንጀል ከመፈፀሙ በፊት እና ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ በሚያከናወናቸው ውጤታማ ተግባራት ድምር ውጤት ነው፡፡ ስለሆነም የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ መሠረታዊ ግቡን ሊያሣካ የሚቻለው

ወንጀል ከመሠራቱ በሚደርገው መከላከልና ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ በሚሠሩት የህግ ሚከበር ሥራዎች እንደሆነ በወል መረዳትና ወንጀል መከላከል ተግባራትን ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡

ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ የሚሠሩት ሥራዎች ላይ ያሉ ክፍተቶችና ችግሮች ከምዕራፍ ሁለት ጀምሮ በዝርዝር ለማሣየት የተሞከረ ሲሆን በዚህ ክፍል በአንደኛ ሁለተኛ ደረጃ የወንጀል መከላከል ሐደት ያሉትን ነጥቦች ለማሣየት ሞከሬአለሁ፡፡

1.2 የመጀመሪያ ደረጃ የወንጀል መከላከል ተግባራት

በፌዴራልም ሆነ በክልል ደረጃ የተቋቋሙት ፖሊስ ኮሚሽኖች አይነተኛ ዓላማ ወንጀል ከመፈፀሙ በፊት መከላከል እንደሆነ የፖሊስ ኮሚሽኖቹ የተቋቋመላቸው የህግ ሜዕቀፎች በግልፅ ደንግገዋል፡፡ ፖሊስ ወንጀል ከመፈፀሙ በፊት የሚሠራው የወንጀል መከላከል ሥራ በርካታ ጠንካራ ጎኖችና አመርቂ ውጠቶችን ያስገኘ ስለመሆኑ አያከራክርም፡፡ ሆኖም በአገር ደረጃ እየተሠራ ያለው የወንጀል መከላከል ተግባር የወንጀል ድርጊትን እና የህብረተሰቡን የወንጀል ስጋት ለመቀነስ በሚቻልበት ደረጃ ደርሷል ወይ? የሚለው ነጥብ ሲነሳ ጉዳዩ የሚያከራክርና ግልፅ ወይይት የሚያስፈልገው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

በዚህ በኩል በፖሊስ በሌሎች ፀጥታ ሀይሎችና በህብረተሰቡ የሚደረገው የዕለት ከዕለት የጥበቃና የቅኝት ሥራ በሚፈለገው ደረጃ ላይ ባለመድረሱ የዕለት ከዕለት ጥበቃን እና የቅኝት ሥራን በማጠናከር ልንቆጣጠራቸው የምንችላቸው ወንጀሎች በተደጋጋሚ የሚፈፀማት አጋጣሚ ሰፊ እንደሆነ የሚያከራክር አይደለም፡ በመሆኑም፣

- የመንግሥት ተቋማት እና የግል የንግድ ድርጅቶች ወንጀል መከላከል ከህሎት ያላቸው የጥበቃ ሠራተኞች በመቅጠር የጥበቃና የክትትል ሥራቸውን ከፖሊስ ጋር በመቀናጀት የሚሠሩበት ጠንካራ አሠራር አለመፈጠሩ
- የመንግሥትና የግል ንግድ ድርጅቶች የጥበቃ ሠራተኞች የሚያደርጉት የጥበቃና የቅኝት ሥራ በተቋሙ አጥር ወስጥ ብቻ የሚወሰን ሣይሆን በአካባቢው እስከ ተወሰነ ሜትር ራድየስ ድረስ ያለውን አካባቢ የሚሸፍንበትና አንድ ችግር ሲያጋጥማቸው የፖሊስን እርዳታ የሚሹበት ሁኔታ አለመመቻቸት
- የመንግሥትም ሆነ የግል የጥበቃ ሠራተኞች የጥበቃና የቅኝት ሥራቸውን በአግባቡ እየተወጡ ስለመሆኑ የፖሊስ ክፍል ወጠጉማ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግበት ሥርዓት አለመኖሩ፡፡
- በመኖሪያ ሠፈሮች ኗሪዎቹ በጋራ ገንዘብ አወጥተው አካባቢውን የሚከታተል የጥበቃ ሠራተኛ የሚቀጥሩበት ወይም ራሣቸው ተራ ገብተው አካባቢያቸውን የሚጠበቁበትና ለዚህም ሥራ ከፖሊስ ከፍተኛ የሆነ ድጋፍና ክትትል የሚገኙበት ሁኔታ አለመኖሩ

- በአጠቃላይ የመንግሥት ተቋማት የግል ድርጅቶች እና ኗሪዎች በቀንም ሆነ በማታ በአካባቢያቸው ጥበቃና ቅኝት ተግባር የሚያጠናክሩበት ወጥነት ያለው የአሠራር ሥርዓት አለመዘርጋቱና በገጠርም ሰብልን፣ ከብቶችን፣ የመኖሪያ መንደር ህብረተሰቡ ከአካባቢ ሚሊሺያ ጋር በመተባበር ጥበቃውን የሚያጠናክርበትና
- የእሪታና የድረሱልን ጩኸት ሲሰማ ፈጥኖ በመድረስ በተባበረ ሁኔታ ወንጀል ሠሪዎችን በቁጥጥር ሥር የሚያውልበት በአጠቃላይ በወንጀል መከላከል ተግባር ውስጥ ህብረተሰቡ በነቃ፣ በታቀደና በተቀናጀ መንገድ የሚሳተፍበት ስልት በመቀየስ የመጀመሪያ ደረጃ የወንጀል መከላከል ተግባራትን በተጠናከረ መንገድ የሚከናወንበት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ወንጀልንና የወንጀል መከላከል ስጋትን ለመቀነስ መሥራት ያስፈልገናል፡፡

- በሌላ በኩል በአንድ አንድ አካባቢ የተጠናከረ ጥበቃና ጥብቅ የፀጥታ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል በሚሉ አካባቢዎች፣ በመንግስት ቢሮዎችና የንግድ ድርጅቶች አካባቢ ጨምሮ ተገን በሚድረግ የሚፈፀሙ አስገራሚ የቤት ሠብሮ ስርቆት፣ ወንጀሎች እየተፈፀሙ መሆናቸው በመንግስት በግል በተቋማት ዙሪያ የሚደረጉ የዕለት በዕለት የጥበቃና የቅኝት ሥራዎች ምን ያህል ደካማ እንደሆኑና የመዘናጋት ችግር ያለባቸው እንደሆኑ ስለሚያሣይ በተለይ የጥበቃ ሠራተኞች የሥራ ኃላፊነታቸው አጓድለው ለሚደርሰው ጉዳት የሚደርስባቸው ተጠያቂነት መላላትና ግልፅ አለመሆን ምክንያት የሚፈጠረውን ችግር ለመቅረፍ የህግ ማዕቀፎችንን በአግባቡ መመርመርና ማሻሻል ወይም በአግባቡ ተፈፃሚ ማድረግ ይጠይቃል፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከተው የመጀመሪያ ደረጃ ወንጀል መከላከል ለማስናወን የሚሥሩ የጥበቃ ፣ የቅኝት ተግባራት ሀላፊነት በተሟላበት መንገድና ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ባሣተፈ ሁኔታ ለማስናወን የፖሊስ ሀይል ግንባር ቀደምነት የመምራትና የማስተባባር ተግባር ለማስናወን የእያንዳንዱን አካባቢ ልዩ ሁኔታ መሠረት ያደረገ ሥራ በየአካባቢያችን መሥራት ይኖርብናል፡፡

1.3 ሁለተኛ ደረጃ የወንጀል መከላከል ተግባራት

ሁለተኛ የወንጀል መከላከል ተግባራት በአንደኛ ደረጃ የወንጀል መከላከል ተግባር ሲፈፀሙ በተደጋጋሚ የታዩ ከስተቶችን በአንድ አካባቢ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ የተፈፀሙ ወንጀሎችን የወንጀሎቹን አይነት፣ የወንጀል አፈፃፀም ዘዴ፣ የወንጀል ሰለባ የሆኑት ግለሰቦች ወይም ንብረት በወንጀሉ የጫረጡሱ ሰዎች የግል ሁኔታ ወንጀል ለሚፈፀም ስለሚደረጉ ዝግጅቶች ሣራዎች የወንጀሎች መደበቂያ ሥፍራ የወንጀል ሠሪዎችን የግንኙነት ሚዛና አደረጃጀት ለማወቅ በቂ የሆነ ሚጃ በማሰባሰብ እና በመተንተን ወደፊት ሊፈፀሙ የሚቻሉ ወንጀሎችን መገመትና ወንጀሎቹ

ከሚፀፀሙው በፊት በህጋዊ መንገድ ጣልቃ በመግባት የወንጀልን የወንጀል ስጋትን ለመቀነስ የሚሠራ የወንጀል መከላከል ተግባር ነው፡፡

ሁለተኛ ወንጀል መከላከል በተለምዶ ከሚደረገው የዕለት በዕለት የጥበቃና የፖትሮል /ቅኝት/ ተግባር የሚለየው ምን አይነት ወንጀሎች በየት አካባቢ መቼ በነማን ሊፈፀም እንደሚቻል አስቀድሞ በመገመት ወንጀሉ ከሚፈፀሙ በፊት በተለያየ መንገድ ጣልቃ መግባትን የሚጠይቅ የወንጀል መከላከል ሥራ ነው፡፡ በዚህ በኩል በአገራችን የአሸባሪዎችን እና ሠርጎ ገቦችን የወንጀል ሥራ ተልዕኮ ሴራና ዝግጅት በመከታተል የወንጀል ዝግጅታቸውን ወደ ተግባር ከመቀየራቸው በፊት በቁጥጥር ሥር በማዋል የተፈፀመው የወንጀል መከላከል ተግባር በአርያነት የሚጠቀስ ተግባር ነው፡፡ ሆኖም አሁንም ቢሆን ሁለተኛ ደረጃ የወንጀል መከላከል ተግባር ለማከናወን እየተሠራ ያለው ሥራ ወንጀልንና የወንጀል ሥጋትን በሚፈለገው ደረጃ ለመቀነስ በሚቻልበት ደረጃ ደርሷል ብሎ ለመገገር የሚቻል አይደለም፡፡

በተለይ ለሁለተኛ ደረጃ ወንጀል መከላከል ሚዛዎችን በአግባቡ ማሰባሰብ በመተንተንና የወንጀል መንስኤዎችን መለየትና የመከላከያ ስልት መቀየስ የሚጠይቅ የወንጀል መከላከል አይነት በመሆኑ

- ስለ ወንጀል ሥራ ዝግጅቶች የወንጀል ሴራ እየተጠነሰሰ ስለመሆኑ ጥርጣሬ የሚያሳድሩ ለየት ያሉ እንቅስቃሰዎች በመለካት ህብረተሰቡ ለፖሊስ ሚዛ የሚሰጥበት ሥርዓት መፍጠር
- የተፈፀሙ እና በፖሊስ የተመዘገቡ ወንጀሎች በክስና በፍርድ ያለቁ የወንጀል ጉዳዮች በየወሩ በስድስት ወርና በዓመቱ ተጠቃልለው የሚያዙበትና የሚጠነትኑበት የወንጀል ሚዛና የጥናት ሜዕከላት በአገርና በክልል ደረጃ በማዋቀር
- ወንጀል ዝግጅቶችን አደረጃጀቶችን እና የወንጀሎች የሚዛ ሚዛ ለማግኘት ጥብቅ የሆነ የሚዛ ክትትል ሥራ ማከናወንና ወጠጋማ ወቅትና ሥፍራ በማጠቅ በህጋዊ መንገድ ጣልቃ በመግባት
- የወንጀል ድርጊት መፈፀም መንስኤ የሆኑት ማህበራዊ መሠረቶች ለምሳሌ ድህነት፣ ሥራ አጥነት፣ የአደንዛዥ ዕፅ እና የአልኮል ሱስ ለማስወገድ የሚችሉ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ፕሮግራሞች በመንደፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ህብረተሰቡ ለተግባራዊነታቸው የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ በሚድረግ ለወንጀል መከላከል ትርጉም ያላቸው ሥራዎችን በማከናወን ወንጀልን እና የወንጀል ሥጋት ለመቀነስ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ በአገርና በክልል ደረጃ የመጀመሪያ ደረጃ የወንጀል መከላከል ተግባራትና ሁለተኛ ደረጃ የወንጀል መከላከል ተግባራት ወጤታማ በሆነ መንገድ ለመፈፀም የሚያስችል እና በዚህ ሂደት የመንግሥትንና የመንግሥት ተቋማት የግል ድርጅቶችና የእያንዳንዱን ሰው ሚና እና ተሣትፎ እንደዚሁም ወንጀልንና የወንጀል ስጋትን የመቀነስ ዓላማ ያላቸው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፕሮግራሞች አይነትና ተፈፃሚ የሚሆኑበትን ስልት በተሟላ ሁኔታ አቅፎ የሚይዝ "የወንጀል መከላከል ስትራቴጅ" መቅረፅና እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የሚፈፀሙ ወንጀሎች አይነትና ባህሪ የወንጀሎች አፈፃፀም እና የወንጀል ሠሪዎች ሁኔታ የተለየ ቅርፅ እና ሚዛክ አየያዝ በመጣበት በአሁኑ ዘመን ይህንን ፈተና እና ችግር ለመቋቋም በሚያስችል አግባብ ወንጀል ለመከላከል የሚያስችል አደረጃጀት አሠራርና ስልት እንደዚሁም ተግባራዊ እርምጃ ለመውሰድ ካልቻልን እስከዛሬ በኖርንበት መንገድ ራሣችንን ከወንጀለኞች ጥቃትና ከወንጀል ሥጋት ለመከላከል የማንችል መሆኑን በሚዳት ተጨባጭ የአመለካከትና የአሠራር ለውጥ ማምጣት ይገባናል፡፡


ምዕራፍ ሁለት

የወንጀል ምርመራ እና ማሸረጃ አሰባሰብ ሂደት

2.1 ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ ስላሉት ሂደቶች

የአንዲት አገር የወንጀል የፍትህ ሥርዓት የህብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት ለማረጋገጥ ከሚሠሯቸው ሥራዎች በሁለተኛው ምዕራፍ የሚረጀው ወንጀል የተፈፀመ መሆኑን ለማወቅ ወንጀል ፈፃሚዎችን ለማነየት፣ ወራጀል ፈፃሚዎችን ለመያዝና ስለ ወንጀሉ አፈፃፀም በቂ ማሸረጃ በማሰባሰብ በፍርድ ተጠያቂ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚሠራው ሥራ ነው፡፡ የአንዲት አገር መንግሥትና ህዝብ ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ የሚሠራቸው ተግባራት የተለያየ የሥራ ድርሻ ተቋማዊ ባህሪና ተልዕኮ ባላቸው አካላት በቅብብሎሽ የሚከናወን ተግባር ነው፡፡

ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ የመንግሥት አካላት የሚከናወኑ ተግባራት ወንጀል ስለመፈፀሙና ስለተጠርጣሪዎቹ መረጃ የመቀበል ሂደት Intake procedure ጀምሮ እስከ ፍርድ አፈፃፀም የሚርስ የየራሣቸው ልዩ ባህሪ የአሠራር ሥርዓት ያላቸው ተግባራዊ ሂደቶችን የሚያካትት ነው፡፡ ሂደቱም


የቅበላ
/Intake/
የምርመራ ማጣሪያ
አሰባሰብ
/ Investigation/
የማጣራት
Screening
Outlet/
የዐቃቤ ህግ
አያስከስስም ውሣኔ
የፍርድ ቤት
የመጀመሪያ ደረጃ
መቃወሚያ ብይን
የወንጀል ክስ
Criminal Charge
ለጊዜው ፋይል
መዘጋት
መከላከል
አያስፈልግም ውሣኔ
መጣት
Trial
ፍርድ
ይግባኝ
ፍርድ አፈፃፀም
በይግባኝ ነፃ መለቀቅ
በፍርድ ነፃ መለቀቅ
ፍርድን በመፈፀም በመከራና
ፈተና መለቀቅ
* በእነዚህ ሐደቶች ሁሉ የምህረት አዋጅ
* ከፍርድ በኋላ ደግሞ ይቅርታ የመጫጫ መንገዶች
እንዲሆኑ መንገዘብ ያስፈልጋል

ከላይ በተገለፀው የተለያየ ሂደት የመመርመር ክስ የማቅረብና የመሟገት፣ የሚሟገትና ፍርድ የመስጠት እና የፍርድ ቤት ትዕዛዝና ፍርድ የማስፈፀም ሃላፊነት ያለባቸው አካላት የሚዛተፉ ሲሆን የዚህ ሁሉ ሂደት እና ተግባር የወንጀል ህጉ ወንጀል ከፈፀሙ ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ሲሆን በተግባር በመቀጣጫነት በማዛየትና የጥንቃቄ እርምጃዎችን በመወሰድ ህብረተሰቡ ሰላምና ደህንነት ማስከበር ግብ የማሳካት ዓላማ ያላቸው ናቸው፡፡

ስለሆነም ከዚህ ቀጥሎ የወንጀል የፍትህ ሥርዓታችን በእነዚህ ሂደቶች በአግባቡ እና ወጤታማ በሆነ መንገድ በሜፀም በኩል ያሉት ጠንካራ እና ደካማ ጎኖችና ክፍተቶች እንዳስሳለን

2.2 የወንጀል ምርመራ ትርጉምና ጠቀሜታ

መንግሥት ወንጀል ምርመራና የወንጀል ክስ የማቅረብ ተግባር ሙሉ በሙሉ በወክልና ለግለሰብ ወይም የህግ ሰውነት ላለው ድርጅት አሳልፎ ለመስጠት የሚይችልበትና በርካታ ምክንያቶች እንዳሉ ግልፅ በመሆኑ ምክንያቶቹን ማዘርዘር አያስፈልግም፡፡

በመሆኑም መንግሥት በአንድ አካባቢ ወንጀል የተፈፀመ ስለመሆኑ አጠርጣሪ ሁኔታዎች ሲኖሩ ጉዳዩን የማጣራት ወንጀል የተፈፀመ ስለመሆኑ መረጃ ሲደርሰው መረጃና ማስረጃ የማሰባሰብና የወንጀል ምርመራ የማከናወን ግዴታና ሀላፊነት አለበት፡፡ ስለሆነም በአንድ አካባቢ ወንጀል ስለሜፀሙ አጠራጣሪ ሁኔታ ወይም ወንጀል ስለሜፀሙ መረጃ ሲደርሰው መረጃውን የሜበል እና የወንጀል ምርመራ ማከናወን የመጀመሪያው ተግባር ነው፡፡ ይኸም መንግሥት የሚያከናውነው የወንጀል ምርመራ የራሱ የሆነ ግብና ዓላማ አለው፡፡ ስለሆነም ስለ ወንጀል ምርመራ መሠረታዊ ግብና ዓላማ ለመረዳት በመጀመሪያ የወንጀል ምርመራ ትርጓሜ ጠቀሜታ ምንድን ነው? የሚለውን ነጥብ አንስቶ መወያየቱ የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

- "የወንጀል ምርመራ" መሠረታዊ ትርጉም ስንመለከት የአሜርኛ ቋንቋ መዘገበ ቃላቶች የወንጀል ምርመራ ለሚለው ፅንሰ ሃሣብ የተሟላ ትርጉም ሰጥተው እናገኝም፡፡ ይህንንም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ኢንስቲቲዩት በ1993 ዓ.ም ባሣተመው መዘገበ ቃላት ለመረዳት ይቻላል፡፡ መዘገበ ቃላቱ "የወንጀል ምርመራ ማለት ሕገ ወጥ የሆኑ ተግባራትን እንደ ሌብነት ግድያና የመሳሰለው ጥፋት በደልና ስህተቶችን የምርመራ ሥራ ማከናወን" ማለት ነው በሜል ቁንፅል ትርጓሜ ሰጥቶት እናገኛለን፡፡ በአንፃሩ በእንግሊዝኛ መዘገበ ቃላቶች ውስጥ የወንጀል ምርመራ /Criminal Investigation/ የሚለውን ፅንሰ ሃሣብ መሠረታዊ ምንነት ልዩ ባህሪያትና ዓላማ የሚያቅፋቸውን ተግባራት ሁለንተናዊ በሆነ መንገድ የሚልፅ ትርጓሜ ተሰጥቶት እናገኛለን፡፡

የወንጀል ምርመራ /Criminal Investigation/ የሚለው ፅንሰ ሃሣብ በእንግሊዝኛ የህግ ማዘገበ ቃላት የሰጠውን ትርጓሜ ስንመለከት "Criminal Investigation is a process of establishing that the crime is committed, identifying and apprehending the suspect, recovering the stoen property if any, and assisting in the prosecution of a person charged with crime' የሚል ትርጓሜ ሰጥቶት እናገኛለን፡፡ ይህንን ትርጓሜ በትኩረት ስንመረምረው የሚከተሉትን መሠረታዊ ነጥቦች ያካተተ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ሀ/ የወንጀል ምርመራ በራሱ ግብ ሣይሆን የግብ ማሣካት ሂደት መሆኑ

- የወንጀል ምርመራ ጎን በጎን የሚፈፀሙ የተለያዩ ተግባሮችን የያዘ የሥራ ሂደት /Process/ መሆኑ ነው፡፡ የወንጀል ምርመራ ማከናወን በራሱ መሠረታዊ ግብ አይደለም፡፡ የወንጀል ምርመራ የተለያዩ ዓላማዎችን ለማሣካት የሚከናወን የሥራ ሂደት ነው፡፡ ለዚህም ነው የወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 12 የወንጀል ምርመራ የሚጀመረው ወንጀል ስለመፈፀሙ ምክንያታዊ ጥርጣሬ ሲኖር መሆኑን የሚነግገው በእኛ አገር የወንጀል ምርመራ መጀመር በራሱ እንደ አንድ ግብ የሚታይበትና በተለይም
  - የወንጀል ባህሪ በሌላቸው የፍታብሔር ጉዳዮች መሣሻ በሚድረግ ተጀምረው ጊዜና ጉልበት ከባከነባቸው በኋላ የሚቋኑ የምርመራ ሥራዎች መኖራቸው
    - ያለበቂ ምክንያት ሰውን በቁጥጥር ሥር ለማዋልና አስሮ ለማቆየት ሲባል ዓርብ ተጀምረው ሰኞ የሚቋረጡ ምርመራዎች
    - ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ ተጠርጣሪውን ፍርድ ቤት በዋስ እስኪለቀው ድረስ የተወሰነ ደረጃ ከተራመደ በኋላ ከዚያ በኋላ የሚዘነጉና ተቋርጠው የሚቋሩ ምርመራዎች መኖራቸው ሲታይ የወንጀል ምርመራ መጀመርን በራሱ መሠረታዊ ግብ አድርጎ የመውሰድ የተዛባ አመለካከት እንዳለ ለመገንዘብ እንችላለን፡፡

ለ/ የወንጀል ምርመራ የሚከናወነው በመጀመሪያ ወንጀል የተፈፀመ መሆኑን ለማጣራት ነው፡፡ የወንጀል ምርመራ ከወንጀል ምርመራ የሚከበቀው ወንጀል ለመፈፀሙ በተለያየ መንገድ መረጃ ሲደርስ በእርግጥ ወንጀሉ የተፈፀመ መሆኑ ወይም መረጃው በሀሰት ተቀነባብሮ የቀረበ የተባለው ወንጀልም ያልተፈፀመ መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡ በእኛ አገር ምርመራ የማከናወን ስልጣን ያለው አካል /ፖሊስ/ ወንጀል ሰለመፈፀሙ ጥቆማ ሲደርሰው የምርመራ ሥራውን በእርግጥ የተባለው ወንጀል ተፈፅሟል ወይስ አልተፈፀመም የሚለውን ነጥብ በማጣራት አይጀምርም፡፡ ይልቁንም ወንጀሉ ስለመፈፀሙ እርግጠኛ ሣይሆንና ማስረጃ ሣያሰባስብ ወንጀሉን ፈፀሙ የተባሉትን ሰዎች

በመያዝ ጥቆማ አቅራቢው ስለጉዳዩ ያወቃሉ ያላቸውን ምስክሮች ቃል በመቀበል ምርመራውን ጀምሮ የሚያጠናቅቅበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡

- በዚህ ምክንያት ወንጀል ፈፅመዋል የተባሉት ሰዎች አላግባብ ተከስሰው ብዙ ጊዜ ከታሰሩ በኋላ ተፈፀመ የተባለው ወንጀል በሀሰት ተቀነባብሮ የቀረበ መሆኑን የተረጋገጠበት ሁኔታ በአማራ ክልል በተለያዩ ደረጃ ያሉ ፍርድ ቤቶች ከሰጧቸው ውሣኔዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ አንድ መረጃና ጥቆማ የደረሰው ፖሊስ የቀረበለትን መረጃ በደፈናው ማመን የለበትም፡፡ በመረጃው የተገለፀው ወንጀል ተፈፅሟል ከሚል መደምደሚያ ላይም ስለጉዳዩ ማሸረጃ ከማሰባሰቡና ከማጣራቱ በፊት መድረስ የለበትም፡፡ ስለሆነም መርማሪው ነፃና ገለልተኛ ሆኖ በመጀመሪያ በእርግጥ ወንጀሉ በትክክል ተፈፅሟልን? የሚለውን ነጥብ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ታዓማኒነት ያላቸውን መረጃዎች በማሰባሰብ ዕውነታውን መፈለግ ይገባዋል፡፡

ሐ/ የወንጀል ምርመራ የሚከናወነው ተጠርጣሪውን ለማሳየትና በቁጥጥር ስር ለማዋል ነው፡፡ ስለሆነም የወንጀል ምርመራ የሚያከናውነው አካል ወንጀል መፈፀሙ ካረጋገጠ በኋላ ተጠርጣሪዎቹን ለማሳየትና ለመያዝ የሚከናወን የሥራ ሂደት ነው፡፡ የአንድ ምርመራ እና የወንጀል የፍትህ ሥርዓት ወጤታማነት ተጠርጣሪዎቹን ለማሳየትና ተጠርጣሪዎቹን በመያዝ አቅም ነው፡፡ በዚህ በኩልም ቀላል የሚባሉ ችግሮች መኖራቸውን የሚያመላክቱ መረጃዎች ስላሉ ትኩረት ሰጥተን ልንሠራ ይገባናል፡፡

መ/ የወንጀል ምርመራ ሌላው ትኩረት በወንጅሉ የተወሰዱ ንብረቶች በአስቸኳይ ተከታትሎ መያዝና ማሸሚላስ ፄምር ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ ከተገለፁት ተግባራት ጎን በጎን በወንጀሉ የተወሰደ ንብረት ለማሸሚላስ በትጋት መሥራትን ይጠይቃል፡፡ ይህንን በአግባቡ ማከናወን ሲቻል ብቻ ነው፡፡ "ማንም ሰው በወንጀል ሥራ ፍሬ ተጠቃሚ ሊሆን አይገባውም" የሚለውን መሠረታዊ መርህ ተግባራዊ ለማድረግ የሞቻለው፡፡

ሠ/ የወንጀል ምርመራ አጥፊውን ለፍርድ ለማቅረብና የሞቻል ማሸረጃ ለማሰባሰብና በወንጀል ክስ፣ የመጣትና የፍርድ ሂደት አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ነው፡፡ እዚህ ላይ አንድ አንድ መርማሪዎች ምርመራው ከተጠናቀቀ ዐቃቤ ሕግ ክስ ካቀረበ በኋላ የወንጀል ምርመራ መሠረታዊ ግብ እንደተሳካ አድርገው በተከሣሽ አቀራረብም ሆነ በምስክሮች አቀራረብ እኛን የሚመለከት አይደለም የሚል ከርከር ያቀርባሉ፡፡ አንድ ምርመራ ተከናውኖ ተከሣሹና ማሸረጃዎች ፍርድ ቤት ቀርበው ተጠየቂ የሚሆን ከሆነ የወንጀል ምርመራ መሠረታዊ ግቡን አያሣካም፡፡ ሌሎች አገሮች ተከሣሽን በመክሰስና ጥፋተኛ ለማስኘት የሚደረገው ዕገዛ የወንጀል ምርመራ አንደኛው

ሂደት እንደሆነ " Criminal Investigation is the process of assisting prosection of the person charged with crime." በማለት ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም የወንጀል ምርመራ የወንጀል የምርመራ መዘገቡን እስከ ማጠናቀቅ ድረስ ያለውን ሂደት ብቻ የሚመለከት አድርገው የሚያስቡና ተከሣሹንና በምርመራ ሂደት የተሰበሰቡትን ማስረጃዎች ለፍርድ ቤት በማቅረቡ ሂደት ምንም አይነት እገዛ ሚድረግ እንደሌለባቸው የሚያስቡ መርማሪ ፖሊሶች " የወንጀል ምርመራን እንደ መሠረታዊ ግብ ማሣኪያ ሂደት ሣይሆን ምርመራ ማጣራቱ በራሱ ግብ አድርገው የሚመለከቱ በመሆናቸው የአመለካከት ለወጥ ሚድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ረ/ የወንጀል ምርመራ ልዩ ባህሪ ያላቸውና የወንጀል ሰለባ የሆኑ ሰዎች በማያዣነት የታገቱባቸው ወንጀሎች ተፈፅመው በሆነ ጊዜ ከላይ ከተገለፁት ተግባራት በተጨማሪ የወንጀል ሰለባ የሆኑትን ሰዎች ከተጋረጠባቸው አደጋ ለማታደግና አስፈላጊውን እርዳታ እንዲያገኙ የሚከናወነውን ተግባር ያጠቃልላል፡፡ የተፈፀመው ወንጀል ሰውን አስገድዶ መነወር፣ ጠልፎ፣ ንፁሐን ዜጎችን ማገትና መደራደሪያ ሚድረግ የመነሰሉት በሆነ ጊዜ ከላይ ከተገለፁት በተጨማሪ የወንጀሉን ሰለባ ለማስለቀቅ የሚከናወኑ ተግባራትን ያጠቃልላል፡፡

2.3 የወንጀል ምርመራ፣ ከመጀመሩ በፊት ጉዳዮችን በጥልቀት ስለመመርመር

ከላይ እንደተገለፀው የወንጀል ምርመራ ማከናወን በራሱ፣ ግብ አይደለም፡፡ የወንጀል ምርመራ የሚከናወነው፡ –

- ወንጀል የተፈፀመ መሆኑን ለማረጋገጥ
- ወንጀል ተፈፅሞ በተገኘ ጊዜ በወንጀሉ የሚጠረጠሩ ሰዎች ለመለየትና ለመያዝ
- የወንጀል ሰራዎችን በፍርድ ተጠያቂ ለማድረግ የሚያስችል ማስረጃ ለማሰባሰብና የክስና የፍርድ ሂደቱን ወጠጉማት ተገቢውን ድጋፍ ለመስጠት
- በወንጀል የተወሰደ ንብረት ተከታትሎ ለመያዝና
- የወንጀል ሰለባ የሆኑትን ሰዎች የመታደግ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

በመሆኑም አንድ መርማሪ በአቤቱታ በጥቆማ ወይም በሌላ መንገድ መረጃ ሲደርሰው የወንጀል ምርመራ ከመጀመሩ በፊት ከመርመራ ሥራው ሲጠናቀቅ ሊሳካ የሚችለው መሠረታዊ ዓላማ ያለ መሆኑን፣

- ምርመራውን ለማከናወን መሟላት ያለበት የህግ ስርዓት እና ሌሎች የህግ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡ መርማሪው ምርመራውን አከናውኖ ሲጨርስ ሊያሳካው የሚችለው መሠረታዊ ግብ የሌለ መሆኑን ወይም የወንጀል ምርመራና ክስ ለማስቀጠል፣

የሚይችሉ በህግ የተደነገጉ ሁኔታዎች ያሉ መሆኑን ከተረዳ ስለ ጉዳዩ በምርመራ በሚከናወን ጊዜውንና ጉልበቱን ከማከኑ በፊት ጉዳዩ ባለበት ስለሚቋርበት ሁኔታ ስልጣን ካለው ዐቃቤ ህግ ጋር መመካከር ይገባዋል፡፡

- እስካሁን የሚከናወኑ ምርመራዎች የሚጨረሻ ውጤታቸው እና ምን ዓላማ ሊያሳኩ እንደሚችሉ፣ ከመጀመሪያው ሳይታሰብባቸው የሚፈፀማ ያለምንም ግብ የሚመሪው ጊዜ ጉልበት እና ገንዘብ ከባከነባቸው በኋላ ምንም አይነት ወጤት ሳያስገኙ የሚቃሩበት አጋጣሚ ቀላል አይደለም፡፡ በመሆኑም የወንጀል ምርመራ ከመጀመሩ በፊት የወንጀል ምርመራ የሚያከናውነው አካል
- ተከሳሹ በወንጀል ኃላፊ በሚሆንበት አግባብ የህግ የግዙፍ ተግባርና የሀሳብ ሁኔታ መሟላታቸውን በጥልቀት አለመመርመር
- ተፈፀመ የተባለው ወንጀል በግል አቤቱታ አቅራቢነት ወይም በመንግስት በኩል ክስ የሚቋርብበት መሆኑን መለየትና በግል አቤቱታ አቅራቢነት የሚያስከስሱ ወንጀል ሆኖ ካገኘው የተበዳዩ ፈቃድና አቤቱታ ሳያገኝ የወንጀል ምርመራ ማከናወን፡፡
- ወንጀሉን ፈፀመ የተባለው ተጠርጣሪ ለወንጀሉ በኃላፊነት የሚጠየቅ መሆኑን አለማረጋጥ
- የወንጀል ክስ ማቅረቢያ ጊዜ በይርጋ ያልታገደ መሆኑን አለማረጋጥ፣
- ለወንጀሉ በኃላፊነት የሚጠየቀው ተጠርጣሪ በህይወት ያለ መሆኑን አለማረጋጥ፣
- ተከሳሹ በጉዳዩ በወንጀል ተከስሶ ጥፍተኛ ሆኖ ያልተቀጣ ወይም በነፃ ያልተሰናበተ መሆኑን ሣያረጋገጡ ምርመራ ማከናወን እና ሌሎችም ጥልቅ ወይይት ሊደረግባቸው የሚገቡ ድክመቶች ናቸው፡፡ ከላይ የተዘረዘሩት ጉዳዮች በትኩረት በማት የወንጀል ምርመራ እየተከናወነ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጥያቄ ሲነሳ በፌዴራልም ሆነ እኔ ከመጣሁበት ክልል የሚፈፀሙ በርካታ ስህቶች እንዳሉ በርካታ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮችን አንስቶ ለማረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም ከላይ ከተገለፁት አንደኛው ሁኔታ ያልተሟላ ከሆነ የሚሰራው የወንጀል ምርመራ ፍሬ ቢስና ዓላማ የለሽ የሚያደርግ በመሆኑ በጥንቃቄ መታየት አለበት፡፡

2.4 ሚጃን እና ማረጃን በጥንቃቄ ማባሰብ

በህግ መዋ የተሰማሩ ሰዎች በተለይም የፍትህ አካላት ባለመዋዎች በአንድ በኩል በወንጀል ምርመራ ሒደት የሚያገኝ "እያንዳንዷ ጥቃቅን ሚጃ የምርመራውን የትኩረት አቅጣጫ ለመወሰን ስለ ወንጀሉ አፈፃፀምና ወንጀል ስለፈፀመው ሰው ፍንጭ ለማፍነፍ ተጠርጣሪዎችን ለመለየትና አጥፊውን ለመፉረድ የሚያስችል ማረጃ ለማገኘት የሚይናቅ ጥቅም ስላለው ሚጃዎችን በጥንቃቄ አሟ

በማሰባሰብና በመተንተን ጥቅም ላይ ማዋል ያስፈልጋል በማለት የሚገሩ ሲሆን በሌላ በኩል በወንጀል በተጠረጠረ ሰው ላይ ክስ ለማቅረብና የጥፍተኝነት ወሳኔ ለማጠት ህጋዊ ተቀባይነት ታዓማኒነትና ከብደት ያለው ማስረጃ ያስፈልጋል ሲሉ ይስማሉ፡፡"
በመሆኑም፡ –

- በመረጃና በማስረጃ መካከል በትርጓሜ በይዘት ደረጃ መሠረታዊ ልዩነት አለ ወይስ የለም?
- በመረጃና በማስረጃ መካከል ያለው መሠረታዊ ልዩነትና አንድነት ምንድን ነው?
- በመረጃ እና ማስረጃ ከማሰጠት ጠቀሜታ አንፃር መሠረታዊ ልዩነት አላቸው ወይ የሚሉትን ነጥቦች ዙሪያ አንድ አንድ ሀሳብ መለዋወጥ ይገባል፡፡
- ስለ መረጃና ማስረጃ ትርጓሜ ይዘት እንድነትና ልዩነት በቂ የሆነ ግንዛቤ ይኖራል በሚል ዕምነት ዝርዝሩን ማቅረቡ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡

ሆኖም አንድ ወጠጉማ ምርመራ ነፃና ገለልተኛ በሆነ እምነትና ስሜት ከተለያየ አቅጣጫ ስለ ጉዳዩ የሚቃርቡለትን ዕርስ በዕርስ የሚቃረኑ መረጃዎች በማሰባሰብና የመረጃዎቹን ትክክለኝነት እና ከጉዳዩ ጋር ያላቸውን ተያያዥነት በማጣራት መጀመር አለበት እዚህ ላይ መረጃ ለወንጀል መላላከልና ለወንጀል ምርመራ ሥራ ያለው ጠቀሜታ በቀላሉ ሊታይ አይገባውም፡፡

በማናቸውም አገር መረጃ መደበኛ በሆነ ሆኔታ በሚቃርብ አቤቱታና ጥቆማ መደበኛ ባልሆነ መንገድና በጥናትና በከትትል ይገኛል፡፡ እዚህ ላይ በምርመራ ሒደት በአገራችን ፖሊስ ከአንድ ጠቋሚ ወይም ምስክር ለማገኘት የሚሞለውን ያህል መረጃ አሟጦ ለመቀበል የሚያስችለውን አሠራር ሳይሆን ጠቋሚው በፅሑፍ አስፍሮ እና ፈርሞ የሰጠውን መረጃ ብቻ ይዞ የሚቃርበትን አሠራር እየተከተለ መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው፡፡

የአገራችን ፖሊስ በየትኛውም አለም በጠቋሚዎች የሚያወቁትን መሉ መረጃ አሟጦ ለመቀበል የሚያስችለውን "Interviewing" ዘዴ በማጠቀም መረጃ በአግባቡ አይሰበስብም፡፡ አሁን በተግባር የሚከናወነው ጠቋሚው በወረቀት አፅፎ መረጃውን ለፖሊሱ እንደሰጠው ሚድረግ ሲሆን ይኸ አሠራር ተቀባይነት ካላቸው ዓለም አቀፍ የመረጃ አቀባበል ስርዓት ያፈነገጠ ብቻ ሳይሆን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ስርዓት ህግ ቁጥር 14 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ጋር የሚቃረን መሆኑን የህጉን ድንጋጌ በማንበብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ የአገራችን የወንጀል ምርመራ ሥራ፡ –

- ስለ ወንጀሉ መፈፀም፣ ስለ ወንጀሉ አፈፃፀምና በወንጀሉ ስለሚጠረጠሩ ሰዎች ነፃና ገለልተኛ ሆኖ ሁሉንም አማራጮች ለማየትና ለመዳሰስ ከሚያስችል አግባብ መረጃዎችን በማሰባሰብ ሳይሆን ቀድሞ አንድ ሚደመደሚያ በመያዝ፣ የሚደመደሚያውን እውነትነት ለማረጋገጥ፣ የሚከናወን መሆኑ፣

- መረጃንና ማስረጃን ማዕከል በሚድረግና ተጠርጣሪው ሳያወቅ ፍንጭ ለማፍነፍ፣ መረጃና ማስረጃ ምንጮችን መሠረታዊ ግብ አድርጎ የሚቀሳቀስ ሳይሆን ተጠርጣሪውን ማዕከል በሚድረግና ማፍቸውንም ፍንጭ ሆነ መረጃ ከተጠርጣሪው ምንጮችን እንደ ግብ ይዞ የሚከናወን መሆኑ፣
- የመረጃን በተሟላ መንገድ ያለማከብሰብ ማስረጃዎችን ህጋዊ ተቀባይነት ከብደትና ታዓማኒነት በሚያጠናክር ሂደት ሳይሆን በሚያዳክም አሰራር የሚከተል መሆኑ፣
- ህጋዊ የሆነ የብርብራና መያዣያ ትዕዛዝ ባልተሟላበት ሁኔታ የተለያዩ ኤግዚቪት የመያዝ ቴክኒካል ማስረጃዎች ተቀባይነት መንገድ ለማስባሰብ ለመመርና ወጤታቸውን ለማቅረብ የሚያስችሉ ከፍተኛ የሆነ የክህሎት የቁሳቁስና ያላብራቶሪ ችግር ያለበት መሆኑ፣
- ነፃና ገለልተኛ የሆኑ ምስክሮችን ቃል ከማስባሰብ ድካም የሚጠይቅ ሥራ ከማከናወን ይልቅ ተጠራርተው የቀረቡ የዘመድ ምስክሮችን ቃል በመቀበል የምርመራ መዘገቡን ለማጠናቀቅ ትኩረት የሚያደርግ መሆኑ፣
- ተቀባይነት፣ ታዓማኒነትና ከብድት ያላቸውን ማስረጃዎች ከማስባሰብ ይልቅ ከጉዳዩ ጋር ይኸ ነው የሚባል ግንኙነት የሌላቸውን ማስረጃዎች በማያያዝ መርካትና የምርመራ መዘገቡን ማጠናቀቅን እንደ ግብ መመልከት፣
- በምርመራ ሒደት ዐቃቤ ህግ መያዊ አስተያየትና ድጋፍ ከማጠየቅ ይልቅ፣ ስለተያዘ ምርመራ እና እየተሰበሰበ ሰላለው ማስረጃ ምንም አያገባውም፣ የእኔ ኃላፊነትና ሥራ ነው በሚል መንፈሰ በመዘገቡ ላይ ወሳኔ ከሚሰጠው አካል፣ መደበቅ የሚከናወን መሆኑ፣
- የምርመራ ሥራውን በሰፊውና አሟጦ ለማከናወን በኩል የፍላጎትም ሆነ የብቃት ችግር የሚስተዋልበት በመሆኑና ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማስኘት በመንግስት በኩል ያለውን የማስረዳት ሸክምና የማስረጃ ብቃት መሳፈርት ሊያሟሏ የሚቻል ማስረጀ ማሰባሰብን መሠረታዊ ዓላማዊ አድርጎ በመወሰድ በኩል የግንዛቤ የአቅም ችግር ያለበት መሆኑ፣
- በአጠቃላይ መርመራ በራሱ ግብ ሳይሆን ተከሳሹን ማዘናዊና ግልፅ በሆነ ችሎት ተሟግቶ ለማስቀጣት የሚቻል ማስረጃ ማሰባሰብና አጥፊው በፍርድ ሂደት ተከራክሮ ተጠያቂ ሚድረግን መሠረታዊ ግብ አድርጎ ያለመያዝ ችግር የሚታይበትና የወንጀል የፍትህ ስርዓታችን ያሉበት ድክመቶች ዋና ምንጭና መሠረት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ስለሆነም የወንጀል የፍትህ ሥርዓታችን ተጠናክሮ ወጤታማ እንደሆን ከተፈለገ የመርማሪዎችን ክህሎት ለማሳደግ የምርመራ ስልታችን በማዳበርና የሚታዩበትን ድክመቶችና ክፍተቶች ለማሻሻል የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን አለብን፡፡
- ለመሆኑ የምርመራ ሥራ ጉድለት ተጠያቂ የሚሆነው ፖሊስ ብቻ ነወይ?

ከላይ በሰፊው ለመግለፅ እንደሞከረው ወንጀል መፈፀመ መረጃ ሲደርሰው መንግስት መረጃ የመቀበልና የወንጀል ምርመራ ሥራ ያከናወናል፡፡ በእርግጥ የወንጀል ጥቆማዎችን የመቀበልና የወንጀል ምርመራ የማከናወን ኃላፊነት የፖሊስና የፖሊስነት ስልጣን ያላቸው ተቋማት የሥራ ድርሻ ቢሆንም ሌሎች የፍትህ አካላት ሚሰትም

- **ዐቃቤ ህግ፡ –** ጥቆማ እና መረጃ በመቀበል ሐደትና የወንጀል ምርመራን በመምራት ቀዳሚ ምርመራ ፍርድ ቤት ማስረጃዎች እንደሰማ ቃላቸው ተመዘግቦ እንዲያዝ በማድረግና በተከሳሾች የዋስ መላቀቅ ጥያቄ ላይ ተገቢውን ክርክር በማቅረብ
- **ፍርድ ቤት፡ –** ምርመራውን ለማከናወን የሚያስፈልገውን የጊዜ ገደብ በመወሰን የመያዣያና የማርበበሪያ ትዕዛዝ በማስጠት የተከሳሽን የዕምነት ቃል በመቀበልና በቀዳሚ ምርመራ የዐቃቤ ህግ ምስክሮችን ቃል መዘግቦ በመያዝ በተጠርጣሪዎች በዋስ የመላቀቅ ጥያቄ ላይ ተገቢውን ብይን በማስጠት፣
- **ሚዛዊ ቤቶች፡ –** ከፍርድ ቤት በሚሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረት ተጠርጣሪዎቹን ፍርድ ቤት ለወሰነው የጊዜ ገደብ በማቆየት በወንጀል ምርመራ ተገቢውን የጥበቃ፣ የክትትል ተግባር በማከናወን፣

የምርመራ ሐደቱ ህጋዊ ስርዓቱን ተከትሎ ቀልጣፉና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲከናወን የበኩላቸውን ድርሻና ኃላፊት አላቸው፡፡ እነዚህ አካላት በምርመራ ሂደቱ የበኩላቸውን ድርሻና ኃላፊነት በአግባቡ የሚወጡ መሆናቸው ወይም የህጉን መሠረታዊ ግብ እና ዓላማ ለማስካት በሚቻል አግባብ ኃላፊነታቸውን የሚወጠበት ሁኔታ መኖሩ በምርመራው ሂደት ቀልጣፉነት፣ ጥራትና ውጤታማት ላይ አወንታዊ ወይም አሉታዊ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው የሚከራከር አይደለም፡፡

በመሆኑም የአገራችን የወንጀል ምርመራ ሥራ ድክመት ሆነ ጥንካሬ የፖሊስ ብቻ ሳይሆን በሂደቱ የተለያየ ድርሻና ኃላፊነት ያላቸው ተቋማትም በጎ ወይም አፋራሽ ሚና እንዳለበት በወል ማየትና እያንዳንዱ ተቋም በምርመራ ሂደቱ ባለው የሥራ ድርሻ ስለሚታዮበት ድክመቶች በግልፅ መጋገር ያስፈልጋል፡፡

ምዕራፍ ሦስት

ስለ ማጣራት የወንጀል ክስ አቀራረብና የመጣት ሒደት

3.1 ስለማጣራት ሂደት በጠቅላላው

የወንጀል ምርመራ ተከናወኖ ማስረጃ ከተሰበሰበ በኋላ የማጣራት ሒደት /screening stage/ በወንጀል የፍትህ ስርዓቱ መካናወን ያለበት ተግባር ነው፡፡ አገሮች እንደሚከተሉት የህግ ስርዓት የማጣራቱ ሒደት፣

- በዐቃቤ ህግ ብቻ እንዲከናወን ስልጣን የሚሰጡ
- በፍርድ ቤትና በሸንጎ /Jury/ እንዲከናወን የሚያደርጉ
- ሁለቱም በማጣራቱ ሒደት ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያደርጉበት ሁኔታ ያጋጥማል፡፡

አሁን ባለን የህግ ሥርዓት በወንጀል ምርመራ የተሰበሰበውን ማስረጃ መዘኖ፡ –

- በተከሳሹ ላይ ክስ የማቅረብ
- በተከሳሹ ላይ የክስ አይቀርብም ውሳኔ ለማሰጠት
- ተጨማሪ ምርመራ እንዲከናወንና ተጨማሪ ማስረጃ እንዲሰባሰብ ትዕዛዝ የማሰጠት ስልጣን ያለው ዐቃቤ ህግ ነው፡፡

ለዚህም ነው በእኛ አገር የህግ ሥርዓት ዐቃቤ ህግ በወንጀል ጉዳዩ የመጀመሪያው የዳኝነት ተግባር የሚከናወን ተቋም ነው የሚለው የወጣት ጥፋተኞችን በሚመለከት ጉዳይና በማስ ወንጀሎች በሚከናወን የቅድመ ክስ ሰሚ ሒደት ካልሆነ በስተቀር በአገራችን የማጣራት ሥራ ማሉ ለማሉ ለዐቃቤ ህግ የተሰጠ ነው፡፡ ሆኖም ወጣት ጥፋተኞች ላይ ከአስር ዓመት በላይ በሚያስቀጣ ወንጀል ክስ ለማቅረብ ዐቃቤ ህግ የፍርድ ቤቱን ፈቃድ ማግኘት እንዳለበት እና በማስ ወንጀሎች ፍርድ ቤት በቅድመ ክስ ሒደት የዐቃቤ ህጉን ክስ ተገቢነት ከመደበኛ መጣት በፊት የማጣራትና ተገቢውን ውሳኔ በማሰጠት የሚተፉበት የህግ ሥርዓት አለ፡፡

በማጣራት ሒደት ዐቃቤ ህግ የፖሊስን የምርመራ መዝገብ በደረሲው በአስራ አምስት ቀን ውስጥ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 38 ከተመለከቱት አንደኛውን መወሰን የሚበቅበት ሲሆን ዐቃቤ ህግ የምርመራ መዝገቡን የሚዘጋባቸው ምክንያቶች በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 39 እና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 42 ተደንግገው እናገኛዋቸለን፡፡

- እዚህ ላይ በማጣራት ሒደት ዐቃቤ ህግ ክስ ለማቅረብ የሚጠቀምባቸው መስፈርቶች ምንድን ናቸው?
- የህግ እና የማስረጃ ሁኔታዎች በተሟሉበት ሁኔታ የህዝብ ጥቅም ማጣሻ በሚድረግ ዐቃቤ ህግ የወንጀል ክስ አላቀርብም በማለት መዘገቡን መዘጋት ይችላል?
- በአገራችን የምትከተለው አስገዳጅ የሆነ የክስ አቀራረብ ስርዓት ነው ወይስ ሰፊ አሚራጭ የሚፈቀድ የክስ አቀራረብ ሥርዓት?
- በአገሪቱ እስካሁን የያዛችውን የማጣራት ሒደት ይዛ መቀጠል ይገባታል ወይስ መለወጥ! አለበት?
- የክስ አቀራረብ ፖሊስ በሌለበት ሁኔታ ክስ ማቅረብ መሠታዊ ግብ ተደርጎ ነው የሚወሰደው ወይስ የግብ ማሳኪያ አንድ መንገድ የሚሉትን ነጥቦች በጥልቀት በማየት የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ በማጣራት ሒደት ያለበትን ጠንካራና ደካማ ጎን መለየት ይጠይቃል፡፡

3.2 በክስ አቀራረብ ሂደት የሚነሱ ችግሮች

በአገራችን የወንጀል የፍትህ ሥርዓት ዐቃቤ ሕግ ከፍተኛ ሚና ስልጣን ያለው አካል ነው፡፡ ዐቃቤ ህግ ሚናውን በአግባቡ መወጣት የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ ውጤታማነት ወሣኝነት አለው፡፡ በመሆኑም በክስ አቀራረብ ሂደት

- ተከሣሹን በሀላፊነት የሚያስጠይቁ እና የሚያስቀጡ ሁኔታዎች መኖራቸውን ከምርመራ መዝገቡ በተያያዙት ማስረጃዎች ማለትም ተከሣሽ ለድርጊቱ ፍፁም ኢ ሀላፊ መሆኑን ፍፁም በሆነ መልኩ የፈፀመው መሆኑን አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ ወይም በሕጋዊ መከላከያ የፈፀመው መሆኑን የሚያሣይ በቂ ማስረጃ እያለው ክስ የሚያቀርብበት ሁኔታ መኖሩ በቀዳሚነት የሚጠቀሰው ሲሆን ፣

ለዚህም ማጣሻው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 42/1/ሀ/ በእንደዚህ አይነት ምክንያቶች ዐቃቤ ሕግ ክስ አያስቀርብም ብሎ ለመወሰን ስልጣን አይሰጠውም የሚል ነው፡፡ ሆኖም የህጉን ድንጋጌ ስንመለከተው "ክስ ለማቅረብ የሚይቻለው ጥፋተኛ ለሚድረግ በቂ የሆነ መረጃ የሌለ መሆኑን ዐቃቤ ሕግ የተረዳ እንደሆነ" የሚል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

- በመሆኑም የተሰበሰበው መረጃ ተከሣሹ በህጋዊ መከላከል ድርጊቱን መፈፀማን የሚያስረዳ በሆነበት ሁኔታ ዐቃቤ ሕጉ ተከሣሹን ከስሶ ጥፋተኛ ለሚድረግ የሚያስችል በቂ ማስረጃ አለው ለማለት ይቻላል?

- ተከሣሹ የፈፀመው ድርጊት በህላፊነት የሚያስጠይቀውና የሚያስቀጣው ሁኔታ መኖሩን በተሰበሰበው ማስረጃ ተረጋግጦ እያለ ዐቃቤ ህግ ዝም ብሎ ክስ ማቅረቡ ምን ጠቀሜታና ፋይዳ ይኖረዋልን የሚሉት ነጥቦች አገራዊ ችግር በመሆናቸው በወል መታየትና አስራሩ መስተካከል ይኖርበታል፡፡
- በሁለተኛ ደረጃ ዐቃቤ ህግ በክስ አቀራረብ ላይ የሚስተዋለው ችግር ዐቃቤ ሕግ ክስ ለማቅረብ የሚያስፈልገው የማስረጃ እና ተከሣሹን ለማስቀጣት የሚያስፈልገው ማስረጃ ደረጃ /Standard of proof/ የተለያየ አድርጎ ማሰብ በደካማ ማስረጃ ክስ የሚመሠረትበት ሁኔታ መኖሩ ነው፡፡ በመሠረቱ የወንጀል ክስ ማቅረብ ብቻ በራሱ ግብ አይደለም፡፡ ስለሆነም ዐቃቤ ህግ ክስ ለማቅረብ በእጁ ያለው ማስረጃ በመጀመሪያ ተከሣሹን የሚየቀርባቸውን መሰላከያ ማስረጃዎች የሚቋቋምና ተከሣሹን ጥፋተኛ ለማድረግ የሚቻል መሆኑን በአግባቡ መመዘንና መመርመር ይኖርባቸዋል፡፡
- ዐቃቤ ህግ ወንጀሉ የተፈፀመበት ጊዜ፣ እና ቦታ በድርጊት እና በወጪት መካከል ምክንያታዊ ግንኙነት መኖሩን አለማረጋገጥ፡፡ በዚህ ምክንያት ያልተሟላ ክስ የማቅርብበት ሁኔታ ያለ መሆኑና በሌላ በኩል ወንጀሉ የተፈፀመበት ጊዜ የሚለው አባባል ፍርድ ቤት ጡበቦ የመተርጎም ችግር መኖር ለምሳሌ አንድ ገንዘብ ያዥ ከመስከረም/1999 እስከ ሰኔ 1999 ከተቀበለው ገንዘብ ወስጥ 50,000 አጉድሏለች የሚል ክስ ሲቀርስ 50,000 ብሩን በየትኛው ቀንና ወር እንዳጎደለች ገልፃችሁ ክሶችን ካላሻሻላችሁ እንቀበልም የሚልበት አጋጣሚ መኖሩ በወል መታየትና መስተካከል ይገባዋል፡፡
- ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች ክስ ሲቀርብ ክሱን በአንድ ላይ ለማቅረብ የሚያስችል ምክንያት መኖሩን አለማረጋገጥ፣ ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች ሊከሰሱ በወንጀሉ ያላቸውን የተሣትፎ ደረጃ በክሱ ወስጥ በአግባቡ ያለመግለፅ ከአንድ በላይ ወንጀል በተፈፀመ ጊዜ እያንዳንዱ የወንጀል ድርጊት ላይ ክስ አለማቅረብ ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡ /የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.117/ ያላሟላ፣
- የወንጀል ፍሬ ሃሣብ የሌላቸው የክስ ማመልከቻዎች ማቅረብ ለመጣትና ለክስ ሰሚ ተፈላጊውን ዝግጅት አለማድረግ ተገቢ ባልሆነ ምክንያት መዛግብትን መዘጋት ምስክሮችን አስቀድሞ ለይቶ አለመጣባት በአጠቃላይ የወንጀል ሰሜ መጣት ወቅት ዐቃቤ ህግ ዕውነቱ እንዲወጣ እና ፍትህ እንዲሰፍን የሚድረግ ግዴታ ያለበት መሆኑን ባገናዘበ መልኩ ኃላፊነትን አለመወጣት በህጉ በተመላከተው የጊዜ ገደብ ውሣኔ አለመስጠትና በሌሎች ችግሮች ወይይት ሊደረግባቸው እና ሊሻሻሉ ይገባል፡፡

3.3 በመጣት ሂደት የሚያዩ ችግሮች

በመጣት ሂደት ዐቃቤ ህግ ተከሣሽና የተከሣሽ ተከላከይ ጠበቃ በተከራካሪነት ፍርድ ቤቶች ደግሞ በብይን ሰጫት በመሟት ይሣተፉ፡፡ የወንጀል የመጣት ሂደት ዳኞች ሊኖራቸው የሚችለው ሚና እንደ አገሮቹ የህግ ሥርዓት የተለያየ ነው፡፡ ስለሆነም ዳኞች በመጣትና ማስረጃ በመመዘን ሂደት፣

- በኮመን ሎው የህግ ሥርዓት
- በሲቪል ሎው የህግ ሥርዓት እና
- ቅይጥ "Mixed" የህግ ሥርዓት

ከሚከተሉት አገሮች የተለያየ ሚና ድርሻ አላቸው፡፡ እዚህ ላይ የእኛ አገር የመጣት ሂደት የሚከራባቸው የሥነ ሥርዓት ህጎች የኮመን ሎው እና የሲቪል ሎው የህግ ሥርዓት የተወሰዱ ቅይጥ የሆነ ባህሪና ይዘት ያላቸው መሆኑን በርካታ አብነቶችን አንስቶ ለማሣየት ይቻላል፡፡

- የመጣት ሂደታቸው ከሁሉቱም የህግ ሥርዓቶች በተቀየጠ ድንጋጌ የሚመሩ አገሮች ተከራካሪዎቹም ሆነ ዳኞች የሁለቱን የህግ ሥርዓቶችና አንድ ድንጋጌ በምን ምክንያት ከሲቪልሎው ወይም ኮከመንሎው እንደተወሰደ ለማወቅ ካልቻሉ ሂደቱ ማዜኑን የሚስትበት ሁኔታ መኖሩ አያከራክርም፡፡ በእኛም አገር የመጣት አካሄድ ሥርዓቱን ለመምራት ታስበው የተደነገጉ የሥነ ሥርዓት ህግ ድንጋጌዎች ከየትኛው የህግ ሥርዓት እንደተዋስናቸውና እንዴት መተርጎምና ሥራ ላይ መዋል እንዳለባቸው በወል ባለመግንዘብ የሚተዋሉ ችግሮች አሉ፡፡ ከነዚህም ጥቂቶቹን ለመግለጽ
    - ዐቃቤ ህግ ክሱን የማረፉት ኃላፊነቱን በአግባቡ የሚይወጣ መሆኑ
    - ዐቃቤ ህግ ከሚመላከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ማስረጃው የማቅረብ ግዴታውን /Burdon of production/ የሚይወጣ መሆኑ
    - ዳኞች በህጉ የተሰጣቸውን የዐቃቤ ህግንም ሆነ የተከሳሹን ምስክር የማጠየቅ መብት ከማጠን አሳልፈው አንድ አንድ ጊዜም ክርክርሩን ገለልተኛ ሆኖ የመምራት ግዴታቸውን እእስከሚስቱ ድረስ የሚጠቀማት መሆኑ፣
    - ዳኞች ዐቃቤ ህግን ምስክሮቹን የማሣትና የማጠየቅ መብት በመደብ ዐቃቤ ህጉን በመተካት ስለሚያወቁት ጉዳይ ማስረጃ ለማሣት የሚጉ መሆኑ፣
    - ዳኞች ተጨማሪ ማስረጃ የማስቀረብና የማሣት ስልጣናቸውን ከህጉ መንፈስና አላማ ውጭ ጥቅም ላይ የሚያውሉ መሆኑ ወይም ስልጣናቸውን ማጠቀም በሚገባቸው ሁኔታ የሚይጠቀሙ መሆኑ፣
    - የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 137/1/ ከመደነግገው ውጭ የሰሚ ሰሚ ማስረጃ ተቀባይነት የለውም በማለት አስቀድመው ወድቅ የሚያደርጉ መሆኑ

በአጠቃላይ ዐቃቤ ህግ የተከሣሽ ጠበቃና ዳኞች የእኛ የሥነ ሥርዓት ህግ ልዩ እና ቅይጥ ባህሪ ባለመረዳት ማዝኑን ከማጠበቅ ይልቅ አንድ አንድ ጊዜ እንደ ኮመንሎው የህግ ሥርዓት እንደሚከተሉት ዳኞች ሌላ ጊዜ ደግሞ የሲስል ሎው የህግ ሥርዓት የሚከተሉትን የመግት አመራር እና አካሄድ በመከተል በተከራካሪዎቹ እና በምስክሮች ላይ ተገቢ ያልሆነ ጫና የሚፈጥሩባቸው ሁኔታዎች በዝርዝር ማጥናት ማስተካከያ ሚድረግ ያስፈልጋል፡፡
በአጠቃላይ በማጣራት የወንጀል ክስ አቀራረብና የመግት ሂደት መመርመርና ማስተካከል ያለባቸው በርካታ ጉዳዮች ያሉ ሲሆን ሁኔታውን የበለጠ ግልፅ ለሚድረግና ለማስተካከል የወንጀል ክስ አቀራረብ ፖሊሲ አወጥቶ በሂደቱ የሚሣተፉ አካላት ተግባራዊ እንዲያደርጉት ሚድረግ ያስፈልጋል፡፡

ምዕራፍ አራት

የወንጀል ፍርድ አሰጣጥና የቅጣት አወሳሰን

4.1 ስለወንጀል ፍርድ አሰጣጥ

የወንጀል ክስ ሰሚኛ የመግት ሒደት ፍርድ ቤት ብይን የሚሰጥባቸው በርካታ ጉዳዮች እንዳሉ ግልፅ ነው፡፡ በወንጀል ሰሚኛ የመግት ሒደት ተከሳሽ በኩል ለማቅርቡ የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያዎች በተከሳሽ ወይም በዐቃቤ ህግ በኩል በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 146 መሠረት የሚቀርቡትን ተቃውሞ ላይ ፍርድ ቤቱ ብይን የሚሰጥ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ህግን ማስረጃ ሰምቶ እና ተቀብሎ ከጨረሰ በኋላ የዐቃቤ ህግ ማስረጃ ተከሳሽን ጥፋተኛ ለሚድረግ ብቃት የለውም ብሎ ሲያስብ ተከሳሹ የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ሣያስፈልገው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141 መሠረት በነፃ እንዲሰናበት ውሣኔ ይሰጣል፡፡

ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ መከላከያ እንዲያቀርብ ብይን ከሰጠ የተከሳሽን የመከላከያ ማስረጃ ከሰማ በኋላ የዐቃቤ ህግንና የተከሳሽን ማስረጃ መዘኖ፣

- ተከሳሹ በዐቃቤ ህግ ባቀረበበት ክስ የፈፀመ ጥፋተኛ መሆኑን ወይም
- ተከሳሽ ዐቃቤ ህግ ባቀረበው ክስ በጠቀሰው የህግ አንቀፅ ሣይሆን በሌላ የህግ አንቀፅ ተላልፎ ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ መሆኑን፣
- ወይም ተከሳሹ በህግ ተጠያቂ የሚሆንባቸው ምክንያቶች በማርዘር በፍርድ በነፃ እንዲሰናበት ይሆናል፡፡

ከላይ የተገለፁት ሐደቶች በዕለት ከዕለት የወንጀል ፍርድ አሰጣጥ ሐደት የሚፈፀሙ በመሆናቸው ለሁላችንም ግልፅ ናቸው፡፡ ሆኖም በፍርድ አሰጣጥ ሐደት ዐቃቤ ህግ ማሸረጃወን እና መሣቱን ህጉ በሚደነግገው አግባብ በማጠቃለል በዐቃቤ ህግም ሆነ በተከሳሽ በኩል የቀረቡት ማሸረጃዎች ህጋዊ ተቀባይነት፣ ታዓማኒነት እና ከብደት በግልፅ በማሣየት በኩል ተገቢወን ትጋት የሚያደርግ መሆኑ፣

- ፍርድ ቤት በዐቃቤ ህግ ክስ የተጠቀሰወን የህግ ድንጋጌ በመቀየር ተከሳሽ ከተከሰሰበት የህግ ድንጋጌ ያነሰ ሀላፊነት በሚያስከትል የህግ ድንጋጌ የመከላከያ ማሸረጃወን እንዲያቀርብ የማሸጠው ብይን ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 113 /2/ መንፈስና ዓላማ አንፃር ተገቢነቱ አከራካሪ መሆኑና ፍርድ ቤቱ ይህነን ብይን ከሰጠ በኋላ ተከሳሹ የፈፀመው ድርጊት በዐቃቤ ህግ ክስ በተገለፀው ድንጋጌ ወይም ከዚያ በላይ በሆነ አንቀፅ የሚያስጠይቀው መሆኑን የሚያረጋግጥ ፍሬ ጉዳይ በራሱ በተከሳሹ የመከላከያ ማሸረጃ ወይም በተጨማሪ ማሸረጃ ቢረጋገጥ የወንጀል ፍርድ በማሸጥበት ጊዜ ፍርድ ቤቱን እንደገና ዐቃቤ ህግ ክሱ ወደጠቀሰው የህግ ድንጋጌ ቀይሮ ጥፋተኛ ለማለት ይችላል ወይስ ቀደም ብሎ በሰጠው ብይን ተገዥ መሆን አለበት የሚል ክርክር ስለማቋረብና በዚህ ዙሪያ የለማይጋጥመወን ተጨማሪ ችግር ለመፍታት በጥልቀት መወያየት ስለማያስፈልግ፡፡

- ዳኞች ዐቃቤ ህግን ማሸረጃ ሰጥተው ተከሳሹ የመከላከያ ማሸረጃ እንዲያቀርብ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/142 ከወሰነ በኋላ ተከሳሽ መከላከያ የለኝም ወይም ለማቅረብ አልፈልግም በሚል ክርክር ሲያቀርብ ወይም ተከሳሽ የቀረበው የመከላከያ ማሸረጃ ህጋዊ ተቀባይነትና ተዓማኒነት የሌለው ሆኖ ብይኑን የሰጡት ወይም ሌሎች ዳኞች ፍርድ በማሸሩበት ጊዜ የዐቃቤ ህግ ማሸረጃ ለምክንያታዊ ጥርጣሬ በር የማክፍት እና ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማሸኘት የማይችል ሆነ ው ቢያገኙት ተከሳሹን በፍርድ በነፃ መልቀቅ ይችላሉ ወይም የዐቃቤ ህግን ማሸረጃ መዘነ ው ተከሳሽ መከላከያ እንዲያቀርብ በሰጡት ብይን የሚቃረን ውሣኔ ላለማጡት ሲሉ በተከሳሽ ላይ የጥፋተኝነት ውሣኔ ይሰጣሉ በሚለው ነጥብ ዙሪያ የተለያየ አቋምና አሠራር በአገር ደረጃ ያለ መሆኑ፣

- በወንጀል ፍርድ በማሸጠበት ወቅት ፍርድ ቤቶች በመጀመሪያ በዐቃቤ ህግ እና በተከሳሽ በኩል ከቀረበው ማሸረጃ ህጋዊ ተቀባይነት ያላቸውንና የሌላቸውን በግልፅ ለይተው የማያስቀምጡ መሆኑና ከተከራካሪዎቹ ማሸረጃ ህጋዊ ተቀባይነት ያላቸውን ማሸረጃዎች በማለየት በመጀመሪያ ታዓማኒነታቸው ከዚያም የማሸረጃወን ክብደት በመመዘን ፍርድ ከማጡት ይልቅ አንድን ማሸረጃ ለምን ወድቅ እንዳደረጉት በማይታወቅበት ሁኔታ በደፈናው ማሸረጃው ወድቅ ነው የሚል ጥቅል አገላለፅ በማጠቀም ውሣኔ የማሸጠበት አጋጣሚ መኖሩ፣

- በወንጀል ፍርድ አሰጣጥ ሒደት የዐቃቤ ህግንና የተከሳሽን የሚረዳት ሸክም በወል ያለማጨዉ የተከሳሽንም ሆነ የዐቃቤ ህግ በህግ በግልፅ በተቀመጠ ግምት መሠረት የሚረዳት ሸክም የሌለባቸዉን ፍሬ ጉዳዮች በትኩረት ሣይመረምሩ ዐቃቤ ህግ ክሱን የሚረዳት ሸክመን አልተወጣም የሚል ምክንያት እየሰጡ ተከሳሹ በፍርድ በነፃ እንዲለቀቅ የሚወሰንበት ሁኔታ መኖሩ፣

አንዳንድ ጊዜ በዐቃቤ ህግ ሚረጃ የወንጀሉ ድርጊት ስለመፈፀሙ ከተገቢው ጥርጣሬ በር በሚይከፍት ሁኔታ ተረጋግጦ እያለ ዳኞች የራሳቸዉን የህሊና ግምት በመመሰድ ተከሳሹ በዐቃቤ ህግ ክስ የተገለፀዉን ወንጀል ስለመፈፀሙ የዐቃቤ ህግ ሚረጃ የተረጋገጠ ቢሆንም የተከሳሹን ሚህበራዊ አቋም መሻሻ በሚድረግ ለምሣሌ ተከሳሽ የመንግስት ባለሥልጣን ከነበረ ካለበት የሥራ ሀላፊነት አንፃር ወንጀሉን ይፈፅሚል ብሎ ለመገመትና አምኖ ለመቀበል ስለሚይቻል በነፃ ተሰናብቷል የሚል የሚረጃ ህግ ሚሆዎችን የሚቃረን ፍርድ የሚሰጠበት አጋጣሚ መኖራቸዉ፡፡

በአጠቃላይ ሚረጃዎችን በሚያያዝ እና በተሟላ ሁኔታ በመሚመር የሚረጃን ተቀባይነት፣ የሚረጃ ታዓማኒነት እና ክብደት በመሚዛን ሒደት ሰፊ የሆነ የግንዛቤና የክህሎት ችግር የሚታይ በመሆኑ ለእነዚህና ሌሎች ችግሮች ዘላቂ መፍትሔ መሻቱት ያስፈልጋል ፡፡

4.2 የወንጀል ቅጣት አወሳሰን

የወንጀል የፍትህ ሥርዓት " ቅጣት" የሚለው ፅንሰ ሀሳብ አንድ ሰው የአንዲትን አገር የወንጀል ህግ በመተላለፍ ጥፋት በመፈፀሙ ምክንያት በመበቱ ላይ የሚጣልበት ሚዕቀብ ወይም የመበት ማጣት ለሚለፅ ቃል ነዉ፡፡ ሆኖም በሚፍቸውም አገር ቢሆን የወንጀል ህግን በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ ሰው ላይ ቅጣት ሲወሰን ጥፍተኛ ሆኖ የተገኘዉን ሰው መበት ላይ ሚዕቀብ መጣል ወይም መበቱን ማጣት እንደሚጨሻ ግብ በማያዝ አይደለም፡፡ ይልቁንም በአጥፊዎች ላይ የሚወሰነዉና የሚፈፀመው የወንጀል ቅጣት መሠረታዊ ግብና ዓላማ የአገርን የመንግስትንና የህብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት ሚከበር ነዉ፡፡

በእኛም አገር በፍርድ ቤቶች የሚሰጠው የቅጣት ውሣኔና አፈፃፀሙ የህብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት ለማከበር የበኩሉን አስተዋፅኦ የሚያበረክት ስለመሆኑ በትኩረት መታየትና መመዛን አለበት፡፡ በአጠቃላይ በጥፍተኞች ላይ የሚሰጠው የቅጣት ውሣኔ በመጀመሪያ ደረጃ ወንጀል ሠሪዎችንም ሆነ ሌሎች ሰዎች ለወደፊቱ ወንጀል ከመፈፀም እንዲታቀቡ በሚድረግ ወንጀልን ለመቀነስና " Detternt Effect" ሊኖረው በሚችልበት አግባብ፣ በሁለተኛ ደረጃ አጥፊዎቹ በፀባያቸው

ጨካኝ አደገኛ ወይም ደጋጋሚ ወንጀለኛ በሆኑ ጊዜ ወንጀለኞቹ ሁለተኛ ወንጀል ለሜፀም እድሉና አጋጣሚው እንዳይኖረው የሚያደርግ ማለትም disablement, incapacitation or preventue punishment የሚለወን ከግንዛቤ ያስገባ በሶስተኛ ደረጃ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የህብረተሰቡን የፍትህ ጥማት የሚያረካና በአራተኛ ደረጃ ጥፋተኛውን ለማረምና የማስተማር ዓላማ የሚያሳካ እና የእነዚህን ጥምር ወጤት ለማምጣት የሚቻል የቅጣት አወሳሰንና አፈፃፀም በማስፈን የህግ የበላይነትንና የህብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት በሚያረጋግጥ አግባብ መከናወን አለበት፡፡

ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ የቅጣት ውሣኔ ሲወስን፡ –

- የህጋዊነት መርህን
- ማንኛውም ሰው ጫካኔ የሞላበት ኢሰብዓዊ ከሆነና አዋጅ ቅጣት እና የቅጣት አፈፃፀም የማጠቅ መበት የማስበር መርህን፣
- የወንጀል ቅጣት በግለሰብ ደረጃ እንጅ አንድ ቡድን ወይም ጎሣ ላይ የጅምላ መወሰን የማታቀብ መርህን፣
- ቅጣቱ ከተፈፀመው ጥፋት ጋር ተመጣጣኝ አድርጎ ሣያንስ ወይም ሣይበዛ "the principle of proportionality " በማከተልና፣
- የአጥፊውን ግላዊ ሁኔታ ያገናዘበ ቅጣት የመወሰን መርህንና
- የወንጀል ቅጣት ለህዝብ ግልፅ በሆነ መንገድ መሰጠት አለበት የሚለውን መርህ በመመርኮዝ መወሰንና ማስፈፀም ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የቅጣት ውሣኔ የሚወሰነው ዐቃቤ ህግና ተከሳሹ ስለ ቅጣት አወሳሰን ያላቸውን የማራከሪያ ሀሳብና ማሸረጃ በመመርመር መሆን ያለበት ሲሆን፣

- በዐቃቤ ህግ በኩል ስለተከሳሹ ያለፈ የህይወት ታሪክ እና ባህሪ መረጃዎች ተጠናቅረው የሚቀርቡ ሲሆን በቅጣት አስተያየትም ሲጠየቅ የወንጀል ህጉን ግብ ለማሣካት የሚቻል አሳማኝ ክርክር በዝርዝር የሚቀርብና ፍርድ ቤቱ የማለወን ቅጣት ቢወስን ቅጣቱን ወይም አቅልሎ ቢወስን ወይም የሜጨሻወን ቅጣት እንዲወሰንበት የሜል አሜርና ጥቅል የቅጣት አስተያየት የሚሰጥ በመሆኑ፣

- ተከሳሹ አጠቃላይ ማህበራዊ የሥነ ልቦናና ሌሎች ሁኔታዎች በጥናት ተከሳሹን ለማረምና ለማስተማር ስለሚቻለው የቅጣት ዓይነት መጀዊ ድጋፍ የሚያደርግ ባለሙያ እገዛ ሣያገኙ ዳኞች የቅጣቱን አይነትም ሆነ ማጠን ለመወሰን የሚደፍበት ሁኔታ መኖሩና ቅጣቱን

ለማሸፈፀም የሚወጣውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ወጪና ኪሣራ ሣይመዘን በሌላ በኩል ጥፋተኛው በቅጣት ውሣኔው መሉ በመሉ ቢፈፀምበትም፣ ጥፋተኛው አትራፊ የሚሆን መሆኑን እና የወንጀል ህጉ መሠረታዊ ግብ የሚያሣካ መሆኑን በማናዘብ በመሰን በኩል የሚታዩ ችግሮች እንዳለ በርካታ አብነቶችን ለማቅረብ ይቻላል፡፡

በመሆኑም በውሣኔ አሰጣጥ ሒደት የሚከተሉት ችግሮች በትኩረት መታየትና መከተካከል አለባቸው፡፡

- በቅጣት ውሣኔ አሰጣጥ የሚታየው የመጀመሪያው ችግር የህጋዊነት መርህ በግባቡ አለመከበሩ ነው፡፡ እዚህ ላይ ፍርድ ቤቶች ቅጣትን በማላቸው አሻሽለው መወሰን እንደሚቻሉ በህጉ ድንጋጌ በግልፅ ባልተደነገገበት ሁኔታ የወንጀል ህጉ ከሚደነግገው ዝቅተኛ የቅጣት ጣራ በመወረድ ለምሣሌ የከባድ የሰው መግደል ወንጀል፣ በከባድ የመግደል መከራ ወንጀልና ጥፋተኛ የተባለን ጥፋተኛ ከአስር ዓመት በታች በመወረድ በአምስት ወይም ሰባት ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ መወሰንና በሌሎችም ወንጀሎች ተመሣሣይ መንገድ በህግ ቅጣቱን ለማቅለል ከተፈቀደላቸው ዝቅተኛ ጣሪያ በታች ሲወስኑ በሰፊው የሚታዩ መሆኑ፣

- በአንድ አንድ አጋጣሚ ቅጣቱን አክብዶ ለመወሰን በህጉ ድንጋጌ ከተገለፀው ቅጣት በላይ የሚወሰንበት አጋጣሚ መኖሩና ዳኞች በወንጀል ሕጉ የተቀመጠውን ዝቅተኛ እና ከፍተኛ ጣሪያ በወል ሣያጤኑ በዘፈቀደ የቅጣት ውሣኔ የመወሰን እንደ በጎ ልምድ አዳብረውት የሚገኙ መሆኑ፣

- ልዩ የቅጣት ማቅለያ ሁኔታዎች ባሉበት ጊዜ በቅጣት አወሳሰን ወቅት ከግምት ወስጥ አለማስገባት በተቃራኒው ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ሁኔታዎችን እንደ ልዩ የቅጣት ማቅለያ ሁኔታዎች በመውሰድ ቅጣቱን አቅልሎ መወሰን፣

- ተደራራቢ ወንጀሎች የተዛመዱ ወንጀሎች እና ጣምራ ወንጀሎች ተፈፅመው በሚገኙበት ወቅት ስለ ቅጣት አወሳሰን ሊሠራባቸው የሚገቡ የቅጣት አወሳሰን ድንጋጌዎችና ባገናዘበ መልኩ የቅጣት ውሣኔ አለመስጠት፣

- የሚወሰኑ የቅጣት ውሣኔዎች አጥፊው ካጠፋው ጥፋት ጋር የሚጣጣም አንድ አንድ ጊዜም ለይስሙላ የቅጣት ውሣኔ የሚሰጥበት አጋጣሚ መኖር፣

- በህግ ከተደነገገው ወጭ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መደብና በህጉ ድንጋጌ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ መደብ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ተከሳሾችን የቅጣት ውሣኔ መወሰንና እንዲፈፀም ሚድረግ፣

- የገንዘብ ቅጣት ለሚከፈፀም በህግ ከተደነገገው ውጭ የእስራት ቅጣትን በአማራጭ ቅጣትነት የመወሰንና የገንዘብ ቅጣቱን ወዲያውኑ ለማስፈል ያልቻለ ተከሳሽ በአማራጭ የእስራት ቅጣት እንዲፈፅም ወዲያውኑ ትዕዛዝ ማስጠት፣፣

- የገንዘብ ቅጣትና ነፃነትን የሚያሣጣ ቅጣት በተወሰነ ጊዜ የእስራት ወይም የፅኑ እስራት ቅጣቱን 2/3 ለፈፀመ ተከሳሽ የገንዘብ ቅጣቱን አልከፈልክም በሚል ምክንያት በአማካሮ እንዳይፈታ ትዕዛዝ ማስጠት፣፣

- ከመደበኛ ቅጣት ውጭ ያሉ ሌሎች የጥንቃቄ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያለመወሰን፣

- በወንጀል ህጉ እና ሌሎች የሥነ ምርዓት ሕግ ሜዕቀፎች የተደነገገው የንብረት እዲወረስ ውሣኔ እንዲሰጡ ሲጠየቁ የህጉን ድንጋጌዎች መሠረት በሚድረግ ውሣኔ አለመስጠት፣

- ከእስር ውጭ ያሉ አማራጭ ቅጣቶችን የወንጀል ህጉን መሠረታዊ ግብ ለማሣካት በሚያስችል መንገድ በአግባብ አለመወሰንና ተፈፃሚ አለሚድረግ፣

በአጠቃላይ ወንጀል አድራጊዎች ከወንጀል ድርጊታቸውን ለማትረፍና የወንጀል የሥራ ፍሬአቸው ተጠቃሚ ለመሆን አስበው የሜፈፅሟቸውን የወንጀል ባህሪያት በመንዘብና ይህንን አመለካከት እና አድራጎት ለማበረታታት ሣይሆን ለመቀንስ የሚያስችል የቅጣት ውሣኔ አለመወሰን እና ሌሎች ከፍተቶችና ችግሮች እንዳሉ የሚያከራክር አይደለም። በመሆኑም ወጥነት የሌለው በዳኞች የግል አመለካከት መሠረት በሚድረግ የሚሰጠውን ፍትሀዊ ያልሆነና ተገማችነት የሌለው የቅጣት ውሣኔ አሰጣጥ ለማስቀረት የቅጣት አወሳሰን ጠቋሚ መመሪያ (Sentencing guidline) በማውጣት ሥራ ላይ እንዲውል ሚድረግና መሠረታዊ የአመለካከትና የአሠራር ለውጥ በማምጣት በፍርድ ቤቶች የሚወሰነው የቅጣት ውሣኔ የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱን መሠረታዊ ግብ ለማሣካት በሚቻልበት አግባብ ማስናወን ያስፈልጋል።

ምዕራፍ አምስት

የወንጀል ፍርድ አፈፃፀም እና ችግሮቹ

5.1 ስለ ሚሜዋ ቤቶች ሀላፊነትና ግዴታ በጠቅላላው

ከዚህ በፊት በጥበቃ ስር ያሉና በፍርድ የ ሰሩ ሰዎች ሰብአዊ መብቶች አያያዝና አጠባበቅ በዓለምአቀፍ ደረጃ የወጡ ህጎችንና የአገራችንን ህግጋት ንደዚሁም በአተገባበር ላይ የሚ ዩ ችግሮ በዝርዝር ቀርቦ ውይይት ተደርጎበ ል፡፡ በ ርግጥ በማረሚያ ቤት ውስጥ በጥበቃ ሥር ያሉና ወይም በፍርድ የ ሰሩ ሰዎች መብትና አያያዝ የሚደነግጉ ዓለም አቀፍም ሆኑ አገራዊ ህግጋት ሲወስኑ በጥበቃ ሥርና በፍርድ የ ሰሩ ሰዎችን መብት የማክበር ግዴ ስላለበት የመንግስት አካል (ተቋምና)
በውስጡ ተመድበው የሚሰሩ ሰዎች ግዴ ና ሃላፊነትም መነሳቱ የማይቀር ነው፡፡ የመብቶችና የግዴ ዎች ትስስር በራሱ በጥበቃ ስር ያሉና በፍርድ የ ሰሩ ሰዎች መብት በአንባሩ በማረሚያ ቤቱና በተÌÑ ሃላፊዎችና ሠራተኞች መብቱን በማሰፈፀም ረገድ ያለባቸውን ግዴ በአንዱ ወይም በሌላው መልኩ የሚያሳይ ነውና ነው፡

ሆኖም የ ስረኞች ሰብአዊ መብቶች አጠቃላይ ይ ብቻውን የማረሚያ ቤቶች የስራ ሃላፊዎችና የማረሚያ ቤት ሠራተኞች በጥበቃ ስር ያሉና በፍርድ የ ሰሩ ሰዎችን አስመልክቶ ያለባቸውን ዝርዝር ህጋዊ ግዴ ና ሃላፊነት ለመረዳት ያስችላል ማለት ንዳልሆነ መጤን ይኖርበ ል፡፡

ማረሚያ ቤቶች በባህሪያቸው የተለያዩ በርµ ሰዎች በተወሰነ የቦ ሥፋት ስብስብ ብለው የሚኖሩበት ተቃማት ናቸው፡፡ በማረሚያ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በሁለት አይነት መንገድ ወደ ማረሚያ ቤቱ የመጡ ናቸው ::
የመጀመሪያዎቹ መንግስት የወንጀል ህጉንና ፍርድ ቤቶች የሚሰጣቸውን ውሳኔዎ ለማስፈጸምና አጥፊዎችን አርሞና አስተምሮ መልካም ዜጋ ለማድረግ ተልዕኮ ባላቸው

የማረሚያ ቤት ተቋማት ውስጥ ተቀጥረው ወይም ተመድበው ለ ራሚዎቹን ተገቢውን መንግስ ዊ አገልግሎቶች የሚሰጡ የማረሚያ ቤቱ የስራ ሃላፊዎችን ሰራተኞች ናቸው። ነዚህ ማረሚያ ቤቱ አወዳድሮ ወይም አሰልጥኖ የሚመድባቸው ተልዕኮውን ንዲያስጽሙለት መርጦና ፈልጎ የሚቀበላቸው ሰዎች ናቸው። ፡

ማረሚያ ቤትን ማረሚያ ቤት የሚያሰኘው በዙሪያው የ ጠረው ረኽርም አጥር በውስጡ ያሉት ክፍሎች ሳይሆኑ የተÌÑN ሰብአዊና ቁሳዊ ሀብቶች (ሪሶርሶች) ለ ቀዱበት ግብ በስርዓት በማንቀሳቀስ ለ ስረኞች አገልግሎት የሚሰጠው የሰው ሀይልና አሰራር መሆኑ ግልፅ ነው። በመጀመሪያው ምድብ y¸µttÜT ይህንን የጥበቃና የማረሚያ አገልግሎት ንዲመሩ የተመደቡ ሃላፊዎችÂ የሚያስተዳድሩዋቸውን አገልግሎት ሰጪ ሠራተኞች#yyz nW።

በሁለተኛው ምድብ የሚካተቱትና የማረሚያ ቤቶቹን አገለግሎት ንዲቀበሉ በፍርድ ቤቶች ት ዛዝ ወይም ውሳኔ ወደ ማረሚያ ቤቶች የማላኩ ናቸው። ነዚህም በግዜ ቀጠሮ የሚመጡ፤በቅጣት ውሳኔ ለአጭር ግዜ ቆይ ወይም ረዘም ያለ የህይወ ቸውን ክፍል ለማሳለፍ የሚመጡና በጥበቃ ስር ቆይተው የተከራከሩ ያሉ ሰዎች ናቸው።በመሆኑም ወደ ማረሚያ ቤት በፍርድ ቤት ት ዛዝ ወይም ውሳኔ የሚላኩ ሰዎች ፈልገውና ወደው ወደ ማረሚያ ቤት ንዳልገቡ ሁሉ ማረሚያ ቤቶችም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የሚላኩ ሰዎችን ተቀበውለው ተገቢውን አገልግሎት ከመስጠት ውጭ ደንበኞቻቸውን የመምረጥ መብትም ሆነ ስልጣን ያላቸውም ።

ማረሚያ ቤቶች በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የሚላኩላቸውን ተጠርጣሪዎች ተከሳሾች ወይም በፍርድ የተቀጡ ሰዎች በቅበላ ሂደቱና ና በማረሚያ ቤት ቆይ ቸው ከማረሚያ ቤቱ ሃላፊዎችና ሰራተኞች ጋር በተለያዩ መንገድ ይገናኛሉ።

በመሆኑም ማረሚያ ቤቶች ንደተቋም መንግስትን በመወከል የ ስረኞችን መብት ና አያያዝ አስመልክቶ ያለባቸው ግዴ ና ሃላፊነት ከዚህ በፊት በቀረበው ጹሁፍ የተዳደሰሰ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በዚህ ፅሁፍ የተያዙ ሰዎችን አስመልክቶ የማረሚያ ቤት ሃላፊዎችና ሰራተኞች ስልጣንና ሃላፊነት በመዳሰስ በዚህ ዙሪያ የሚ ዩ ችግሮችንና ችግሮቹንም ለመፍ ት የሚበጁ የመፍትሄ ሀሳቦችን በማንሳት የሴሚናሩ ተሳ ፊዎች ውይይት ንዲያደረጉ መጋበዝ ነው።

በመሆኑም በዚህ ጽሁፍ በ ስረኞችና በማረሚያ ቤት ሃላፊዎችና ሠራተኞች መካከል የሚኖረውን ግንኙነት በህግ ለመቆጣጠርና የስነ ሥርዓትና የዲስፕሊን ጥፋቶች አፈጻጸም ክትትልና ቁጥጥር ስርዓትን አስመልክቶ ትኩረት የሚሹ ነጥቦችንና ሌሎች በአያያዝ ና በጥበቃ ዙርያ ሊወሰዱ በሚገባቸው ርምጃዎች ላይ አንድ አንድ መሰረ ዊ ነጥቦችን በውይይት መነሻነት ያቀረብኩ ጽሁፍ ናንተ በም ደርደጉት ነጻና ግልጽ ውይይት የበለጠ ንደሚዳብር ያለኝና ተስፋ ገልፃለሁ።

5.2 የማረሚያ ቤቶች ተልዕኮዎችና የአፈፃፀም ችግሮች

5.2 የማረሚያ ቤቶች ተልዕኮ

አገራችን ማረሚያ ቤቶች በህግ ዕውቅና ያላቸው ተቋማት ሆነው አገልግሎት መሰጠት ከጀመሩበት ከ1936 ዓ.ም ጀምሮ አሁን ስካለንበት ጊዜ ድረስ የማረሚያ ቤቶች ተልዕኮ ከባድና ውስብስብ ስለመሆኑና ተቋማቱ ተልዕኮቸውን ለመወጣት ስለሚያስፈልጋቸው ተቋማዊ ብቃትና አደረጃጀት፤የተቋÑ s‰t®C XWqTÂ KHlÖT bmNGST xµ§TM çn bHBrtsbù የተሟላና ትክክለኛ ግንዛቤ ንደሌላቸው በርካ ማጠቀሻዎችንናና ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል።

በ ርግጥ አሁን የሚ የው የተሳሳተ ግንዛቤ ምንጩ ባለፈው ስርዓት የነበሩት መንግስ ት ስለወንጀል ና በወንጀል ስለተጠረጠሩ ፤ ስተከሰሱ ሰዎችና በፍርድ ስለተቀጡ ሰዎች መብትና አያያዝ ያራምዱት የነበረው አሰራርና ና ህብረሰተሰቡ ስለወንጀልና ስለወንጀል ሰሪዎች የነበረው የተሳሳተ ግንዛቤ ነጸብራቅ ነው። ያለፉት መንግስ ት በተለያየ ወንጀል ተጠርጠረው የሚያዙ፤ የማkሰሱና በፍርድ የሚ ሰሩ ሰዎች ሰብአዊ ክብራቸው በተጠበቀበት አኩዋሃን የማይያዙና ለከፋ አያያዝም የተጋለጡ ስለነበር መንግስ ቱ ለማረሚያ ቤቶች ትኩረት ሰጥተው ተቋማዊ አቅማቸውን ለመገንባትም ሆነ ለማሳደግ ያደረጉት ጥረት ንደሌለ የማይካድ ጉዳይ ነው።

በወቅቱ የነበሩት መንግስ ት ስለ ማረሚያ ቤቶች ያራምዱት የነበረውን አስተሳሰብ ለመረዳት ለመጀመሪያ ጊzø ማረሚያ ቤቶችን በአዋጅ ያቋቋመውን **የወህኒ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 45/1936** መመርመሩ ብቻ በቂ ነው፡ ወህኒ ቤቶች አጥፊዎች ሰብዓዊ ክብራቸውን በሚያስጠብቅ ሁኔ ተይዘውና ርመውና መልካም ዜጋ ሆነው የሚወጡባቸው ተቋማት ንዲሆኑ ስበው ያልተቋቋሙና በዚሁ አግባብ ያልተደራጁ ነበሩ ። በመሆኑም በጥበቃ ሥር ያሉ ና በፍርድ የ ሰሩ ሰዎች ለከፋ አያይዝ

የሚጋለጡባቸውና በዚህም ምክንያት የአካልና የስነልቦና ጉዳት ደርሶባቸው የሚወጡባቸው ተቋማት የነበሩ መሆናቸው የሚካድ አይደለም።

ከዚህ በተጨማሪ ተቋማቱ ከነበራቸው ጉድለት በላይ በጥበቃ ሥር ያሉና በፍርድ የ ሰሩ ሰዎች በማሪሚያ ቤቱ አስተዳደሩ ሹም ውሳኔ በሰበብ አስባብ ለአካል ግርፋት ይጋለጡ የነበረ ሲሆን ይህም በወህኒ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 45/1936 ከሴቶችና ከሀምሳ ዓመት በላይ ከሆናቸው ስረኞች በስተቀር የማረሚያ ቤት አስተዳደር ሹም ሌሎች ስረኞችን በአካል ግርፋት ቅጣት መቅጣት የሚያስችለውን የህግ ደንጋጌ መነሻ በማድረግ ይከናወን የነበረ መሆኑ መረጃዎች ያመለክ ሉ።

ይህ ሰብአዊነት የጎደለው አሰራር በህብረተሰቡ ስካሁን ድረስ ንደ ጥሩ የወንጀለኛ መቅጫ ና ማስተማርያ ርምጃ ተደርጎ መወሰዱን በወንጀል የተጠረጠሩ ፤የተከሰሱ ወይም በፍርድ የተቀጡ ሰዎች ማረሚያ ቤት ሲገቡ ለኑሮ ጅግ አስቸጋሪና ከባድ ፈተና ሊያጋጥማቸው ንደሚገባ በመግለጽ አሁን ያሉት ማረሚያ ቤቶች ሆቴሎች ሁነዋል ብለው የሚከራከሩ በርካ ሰዎች ንዳሉ በማየት ለመረዳት ይቻላል።

ከዚህ መሰረ ዊ የሆነ የአመለካከት ችግር አንዳንድ የማረሚያ ቤት የስራ ሃላፊዎች የጥበቃ ሠራተኞችና ሌሎች ሠራተኞች ነፃ ንዳልሆኑ የቀድሞውን አሰራር በድርጊቶቻቸው የሚያንፀባርቁበት ሁኔ ንዳለ ለ ናንተ መንገር ለቀባሪው ማርዳት ይሆናል። በመሆኑም የማረሚያ ቤት የስራ ሃላፊዎችና ሰራተኞች የ ስረኞችን ሰብአዊ አያያዝና አስመልክቶ ያለባቸውን ሃላፊነት ለመተንተን በመጀመሪያ የማረሚያ ቤቶች ተልዕኮና ሃላፊነት ላይ የጋራ ግንዛቤ መያዝ ያስፈልጋል።

- የማረሚያ ቤቶች የመጀመሪያው ተልዕኮ በፍርድ ቤቶች የተሰጡ ትዕዛዞችን የቅጣት ውሳነዎችን በአግባቡ ማስፈጸም ነው። ይህም ማለት ማረሚያ ቤቶች በራሳቸው የሚወስኑት የወንጀል ቅጣት የለም ማለት ነው ። ነገር ግን በፍርድ ቤቶች የተወሰኑትን ቅጣቶች በህግ አግባብ በማስፈጸም የህብረሰተሰቡን፤ የአገርንና የመንግስትን ሰላምና ደህንነት የማስከበር ከፍተኛ የሆነ ህዝባዊ ሃላፊነት ያለባቸው ተቋማት ናቸው።

- .ማረሚያ ቤቶች የፍርድ ቤቶችን ትዕዛዝና ውሳኔ በማስፈጸም የህብረተሰቡን፤ የአገርና የመንግስትን ሰላምና ደህንነት የማስከበር ተልዕኮቸውን የሚወጡት በጥበቃ ስር ያሉና በፍርድ የ ሰሩ ሰዎች በማረሚያ ቤት በሚቆዩበት ጊዜ
  - ጊዜያቸውን፤ ጉልበ ቸውንና ዕውቀ ቸውን ገንቢ የሆነ ስራ ላይ ንዲያውሉ በማድረግ በቴክኒክና በቀለም ትምህረት ንዲጎለብቱ በማድረግ

- በቂ የማህበራዊና የስነ ልቦና ምክር አገልግሎት በመስጠት አጥፊዎች ርመውና መልካም ዜጋ ሆነው ንዲወጡ በማድረግ ነው።

ስለዚህም ነው የማረሚያ ቤቶች ዋነኛውና አብይ ተግባር አጥፊዎች በቂ በሆነ የተሀድሶ አገልግሎት አግኝተው፤ ከጥፋ ቸው ተፀፅተው መልካም ዜጋ ሆነው ንዲወጡ በማድረግ ድጋጋሚ ወንጀለኝነትን በመቀነስ የህብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት ማረጋገጥ ነው።

- . ማረሚያ ቤቶች የፍርድ ቤቶችና ትዕዛዝ ውሳኔ ሲየስፈፅሙ በጥበቃ ስር ያሉና በፍርድ የ ሰሩ ሰዎችን መሰረ ዊ ሰብዓዊ መብቶች ማክበር ማስከበር ሌላው ሃላፊነ ቸው ነው። በጥበቃ ስር ያሉና በፍርድ የ ሰሩ ሰዎች በህግ መንግስቱ አንቀፅ 19 ና 20 ከተረጋገጠላቸው ስነስርዓ ዊ መብቶች በተጨማሪ የአካል ደህንነት መብ ቸውን ከማንኛውም ኢሰብአዊ ና ጭካኔ ከሞላበት አያያዝ የመጠበቅ መብ ቸው፤ ሰብአዊ ክብራቸውን በሚያስጥበቅ አካ ን የመያዝ መብ ቸው ፤ከቤተሰቦቻቸው፤ ከጓደኞቻቸው ና የህግ ጠበቃቸው ጋር የመገናኘ ት መብት ንዳላቸው የህግ መንግስቱን አንቀጽ 16 አንቀጽ 18 ና አንቀፅ 21 ድንጋጌዎች በማየት ለመረዳት ይቻላል።

በአጠቃላይ አሁን ባለንበት ዴሞክራሲያዊ ና ህገ መንግስ ዊ ሥርዓት ወስጥ የማረሚያ ቤቶች ተል ኮና ሃላፊነት የፍርድ ቤቶችና ትዕዛዝ ና ውሳኔ በማስፈጸም የህብረሰቡን የአገርንና የመንግስት ደህንነትና ሰላም ለማስከበር የሚያስችሉ የጥበቃ ፤የተሀድሶና የትምህርት አገልግሎት በጥበቃ ሥር ላሉና በፍርድ የ ሰሩ ሰዎች ሰብአዊ ክብራቸውን በሚያስጠብቅ አኩዋ ን በመያዝ አጥፊዎች ርመውና መልካም ዜጋ ሆነው ንዲወጡ ማድረግ ነው። የማረሚያ ቤት የሥራ ሃላፊዎች ሌሎች ሰራተኞ ይህንን ተልዕኮና ና ሃላፊነት ለመወጣት በሚደርጉት ተግባራዊ ንቅስቃሴ ውስጥ በርካ ችግሮችና ፈተናዎች ያጋጥሟቸዋል። ሆኖም ችግሮቹና ፈተናዎቹ ምንጭና ክብደትና መፍትሔዎች የተለያየ ና ደረጃ በደረጃ ሊፈቱ የሚችሉ በመሆናቸው ከዚህ አንጻር ችግሮቹን ማየትና ለመፍ ት ጥራት ማድረግ ይገባቸዋል።

5.3 ማረሚያ ቤቶች ተልዕኮቸውን ለማስፈጸም ሂደት የሚያጋጥማቸው ችግሮች

ማረሚያ ቤቶች በጥበቃና በፍርድ የ ሰሩ ሰዎች ነጻነ ቸውን በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በማግኘ ቸው ምክንያት ሊገደቡ የማይችሉና መሠረ ዊ ሰብአዊ መብቶች በተሟላ ሁኔ ማረጋገጥ የፍርድ ቤቶችን ትዕዛዝ ና ውሳኔ የማስፈጸምና አጥፊዎችን አርመውና አስተምረው መልካም ዘጋ የማድረግ ከባድ ሃላፊነት ያለባቸው ተቋማት

ናቸው። ከዚህ አንፃር ማረሚያ ቤቶች በጥበቃ ሥር ያሉና በፍርድ የ ሰሩ ሰዎችን ሰብአዊ ክብር በሚስጠብቅ ሁኔ ለመያዝ የአለባቸው የመኖሪያ ወይም መኝ ክፍል ና የቁሳቁስም ጥረት የምግብ አቅርቦትን የጤና አጠባበቅ የህክምና አገልግሎትና በጥበቃ ስር ያሉ በፍርድ የ ሰሩ ሰዎች በሌላ ለይቶ በማስቀመጥ የቤተሰብ ጥያቃና የጉብኝት ፈቃድን በተመለከተ ያሉባቸው መሰረ ዊ የሆነ የተቋማዊ አቅም ማነስ የበጀት ሌሎች ችግሮ ከዚህ በፊት በቀረበው ጹሁፍ በሰፊው ቀርበው ውይይት የተረገባቸው በመሆኑ በድጋሚ ማንሳት አስፈላጊ አይደለም። በመሆኑም ማረሚያ ቤቶች በዕለት ከዕለት የሥራ ንቅስቃሴቸው ሊፈጽሙቸው የሚገባቸውን ውስብስብና ከባድ ህጋዊ ጉዳዮች ለመወጣት ያለባቸውን ሌሎች ችግሮች ላይ በማተኮር አቀርባለሁ።

5.3.1 ማረሚያ ቤቶች በወንጀል ህጉን ባለመረዳት የሚፈጥራቸው ችግሮች

ማረሚያ ቤቶች በፍርድ ቤት የተሰጡ ትዕዛዞችንና ውሳኔዎችን የማስፈጸም ሃላፊነት ያለባቸው ሲሆን ውሳኔውን በማስፈጸም ሂደት የተለያዩ ተግባራት ና ሃላፊነቶች በማረሚያ ቤት አስተዳደር ማቋቋሚያ አዋጅ ብቻ ሳይሆን በኢትየዮጵያ የወንጀል ህግ በሰፊው ተዘርዝረዋል። ማረሚያ ቤቶች የህጎቹን ድንጋጌ መሰረ ዊ ግብና ዓላማ ባለመረዳት አንድ አንድ ጊዜ ህጎቹን ከወጡበት ዓላማ ውጭ ተፈጻሚ በማድረግ በአንድ በኩል የህብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት የማስጠበቅ ተልኳቸውን በአግባቡ ንዳይወጡ የሚያደርጉ በሌላ በኩል በፍርድ የ ሰሩ ወይም በጥበቃ ስር ያሉና ሰዎች መብት የሚጥሱ ተግባራት የሚፈጽሙበት ሁኔ ይስተዋላል። ነዚህም በድምሩ ለማየት፡-

ሀ. ማረሚያ ቤቶች ወንዶችን ከሴቶች በመለየት በፍርድ የ ሰሩ ሰዎችን በጊዜ ቀጠሮና ክሳቸው በመሰማት ላይ ካሉት ሰዎች በመለየት በፍ ብሔር ጉዳይም የ ሰሩት በወንጀል ጉዳይ ከ ሰሩት በመለየት የጥበቃና የተሀድሶ አገልግሎ ቸውን መስጠት ንዳለባቸው በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ህግጋት ብቻ ሳይሆን የኢፌድሪ የወንጀል ህግም ይደነግጋል። በርካ ማረሚያ ቤቶች የማደሪያ ክፍሎቻቸው ጠባብ በመሆኑና አሰራራቸውም ሰዎችን በዚህ አይነት ለመለየት የማያስችል በመሆኑ የወንጀል ሕጉ ድንጋጌ ላለማክበራቸው አንድ መሰራ ዊ ምክንያት በማንሣት ያቀርባሉ በ ርግጥም ለዚህ ችግር ምንጩ በማረሚያ ቤቶቻችን አደረጃጀት ላይ ያለው ከፍተኛ ችግር ንደሆነ ለማስተባበል አይቻልም።

ይህ ንዳለ ሆኖ የህጉን ድንጋጌ በአግባቡ ባለመገንዘብ የሚፈጽሙት ስህተት ንዳለ መገንዘብ ያስፈልጋል።። ይኸውም የስራ ባህሪያቸው በጥበቃ ስር ካሉና በፍርድ ከ ሰሩ ሰዎች ጋር ግንኙነት ያለው የመንግስት ሰራተኛ የነበሩ ሰዎች ወንጀል ሰር ችኋል

በሚል ጥርጣሬ ሲጠየቁ ሲከሰሱ ወይም በፍርድ ሲቀጡ ማረሚያ ቤቶች በወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 110/3/ የተጣለባቸውን ሃላፊነት ባለመወጣ ቸውና በጥበቃ ስር ወይም በፍርድ በ ሰሩ የመንግስት ሠራተኛ የነበሩ ሰዎች ላይ ከፍተኛ መብ ቸውን ክብራቸውን የሚነካበት ሁኔ ንዳለ በርካ ክስተቶች በአብነት ማንሣት ይቻላል።

ህግ አውጪው የመንግስት ሰራተኛ የነበሩ ሰዎች የሚሰሩት ስራ በባህሪው ከ ስረኞች ጋር የሚያገናኛቸው ከነበረ በጥርጣሬ ሲያዙ፤ በወንጀል ሲከሰሱ፤ ወይም በፍርድ ሲቀጡ ከሌሎች ስረኞች ተለይተው መያዝ ንዳለባቸው በግልጽ ይደነግጋል። ዚህ ላይ የወንጀል መከላከል ወይም በወንጀል ምርመራ ስራ በመሥራት በማረሚያ ቤቱ ውስጥ ካሉ ሰዎች ጋር የስራ ግንኙነት የነበራቸው ፖሊሶች በጥበቃና በተሀድሶ ስራ ተሰማርተው በማረሚያ ቤት ሲያገለግሉ የነበሩ የማረሚያ ቤት ሃላፊዎች፤ ፓሊሶችና ሌሎች ሰራተኞች በተለያየ ደረጃ የወንጀል ጉዳይ አይተው ትዕዛዝ ይሰጡ የነበሩ ና ውሳኔ ይሰጡ የነበሩ ዳኞች በወንጀል ተከስሰው ወይም ተፈርዶባቸው ወደ ማረሚያ ቤት በሚላኩበት ጊዜ ማረሚያ ቤቶች በወንጀል ህጉ አንቀፅ 110/3/ የተደነገገውን ለመፈጸምና የ ነዚህን ሰዎች ሰብአዊ ክብር ለማስጠበቅ ባላቸው አቅም ባመሞከራቸው በጥበቃ ስር ያሉና በፍርድ የ ሰሩ ሰዎች መብት የሚጣስበትና ይኸም በተመሳሳይ ሙያና ሃላፊነት ተሰማርተው ባሉ ሰዎች የስራ ሞራል ላይ ከፍተኛ የሆነ ተጽዕኖ ያደረሰ በመሆኑ በትኩረት ሊ ይ ሊፈ የሚገባው ችግር ነው።

ለ/ ማረሚያ ቤቶች ዋናው ተልዕኮ በፍርድ ቤቶች የሚሰጡ ፍርዶችና በአግባቡ ማስፈጸም ነው። ከዚህ አንጻር ማረሚያ ቤቶች በተለይ ፍርድ ቤቶች የሚሰጣቸው ነፃነትን የሚያሳጡ የቅጣት አይነቶች ልዩነት ተረድተው ቅጣቶቹን በማስፈጸም በኩል ስካሁን ሊፈቱት ያልቻሉት ችግር ንዳለባቸው ይህም የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱን ውጤ ማነት በማዳከም ረገድ የበኩሉን ድርሻ የተጫወተ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል።

ፍርድ ቤቶች ሁለት አይነት ነፃነትን የሚያሳጣ ቅጣት ይወስናሉ። ነዚህም በቀላል የ ስራት ቅጣት ና ፅኑ የ ስራት ቅጣት ናቸው።

አንድ ሰው ለተወሰነ ወራት ወይም ዓመ ት በቀላል ስራት ቅጣት ንዲቀጣ የሚወሰነው ወንጀሉ ቀላልና በህብረተሰቡና በአገር ሰላምና ደህንነት የሚያስከትለው ጉዳት ቀላል መሆኑን በማየትና በመመዘን መሆኑን የወንጀል ህጉ አንቀጽ 106 የሚያደነግግ ሲሆን የፅኑ ስራት ቅጣት የሚወሰነው ወንጀል ለማህበረሰቡ አደገኛ በመሆኑና ጥፋተኛው በቀላል ስራት ከተቀጡት የተለየ መሆንና በተለየ ሁኔ መያዝና ከባድ መሆን ንዲሚገባው የወንጀል ህጉ አንቀጽ 108 ይደነግጋል።

ከዚህ በተጨማሪ ቀላልና የ ስራት ቅጣትና ፅኑ የ ስራት ቅጣት አንድ አይነት አለመሆናቸውን ሕጉ አንድ ሰው የጽኑ ስራት ቅጣት የሚስቀጣ ወንጀልና የቀላል አስራት የሚስቀጣ ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ቅጣቱን አጠቃልሎ ለመወሰን ፍርድ ቤቱ የሁለት ዓመት ቀላል የ ስራት ቅጣት ንደ አንድ ዓመት የጽኑ ስራት ቅጣት በመውሰድ ቅጣቱን ደምሮ መወሰን ያለበት መሆኑን የወንጀል ህጉ አንቀጽ 184/1/ ይደነግጋል።

ከ ነዚህ የህግ ድንጋጌዎች የምንረዳው ህጉ በቀላል ስራትና በጽኑ ስራት ቅጣት መካከል ከፍተኛ የሆነ ልዩነት የሚያበጅ ሲሆን በማረሚያ ቤቶች በኩል በሚደረገው ጥበቃ ና አያያዝ የጽኑ ስራት ቅጣት ከቀላል ስራት ቅጣት የተለየና ህጉ በሚያዘው መሠረት የተፈጸመ አይደለም። ይህ ደግሞ በአገራችን ጽኑ ስራት ፍርድ የማስፈራራት አቅም የሚሳጣው ሲሆን ህብረተሰቡም ሆነ በፍርድ የተቀጡት ሰዎች በጽኑና ቀላል ስራት መካከል ያለውን ልዩነት ለመገንዘብ የማያስችል% የወንጀል ህጉን መሰረ ዊ ዓላማና ግብ ዋጋ የሚያሳጣ በመሆኑ በተለይ በሚሰጣቸው የስራ አይነትና የስራ ሰዓት በሚደረገው ጥበቃና በሌሎች ሁኔ ዎ በጽኑ ስራት የተቀጡት በቀላል ስራት ከተቀጡት በተለየ በከባድ ሁኔ መያዝና ህጉን ተግባራዊ ለማድረግ መስራት ይገባል።

ሐ/ በፍርድ ቤቶች የሚሰጡ የጽኑ ስራት ወይም የቀላል ስራት ቅጣቶች ከገንዘብ ቅጣት ጋር ተጣምረው የሚሰጡበትን የፍርድ ቤት ውሳኔ ያጋጥማል። የቀላል ወይም የጽኑ ስራት ቅጣት ከገንዘብ ቅጣት ጋር ተጣምሮ በተወሰነበት ወቅት ለምሳሌ አንድ ሰው ፍርድ ቤቱ በአንድ ዓመት ስራትና በአንድ ሺ ብር የገንዘብ መቀጫ ሊወሰንበት ወይም የስድስት ዓመት ጽኑ ስራትና የአስር ሺህ ብር መቀጫ ቢወሰንበት ማረሚያ ቤቶች ማስፈጸም የሚችሉትን የ ስራትና የጽኑ ስራት ቅጣት በማስፈጸም ፍርደኛው በአመክሮ ለመፍ ት ብቁ ከሆነና ከ ስራት ወይም ጽኑ ስራት ቅጣት ሁለት ሶስተኛውን ከጨረሰ የአመክሮ ጥያቄን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ሲገባቸው ስምንት ወር ስራቱን የፈጸመውን ሰው ፍርድ ቤቱ የወሰነብህን አንድ ሺህ ብር ካልከፈልክ የአመክሮ ጥያቄ አናቀርብልህም ወይም የአራት ዓመት ጽኑ ስራቱን የፈጸመውን ሰው ፍርድ ቤቱ የወሰነብህን ስድስት ሺህ ብር ካልከፈልክ የአመክሮ ጥያቄ አናቀርብም በማለት በተለይ ፍርድ ቤቱ የወሰነውን የገንዘብ ቅጣት ለመክፈል ያልቻሉ ሰዎች ድህ በመሆናቸው ምክንያት ብቻ የተወሰነባቸውን ቅጣት ሙሉ በሙሉ ንዲፈጽሙ በማድረግ በአመንክሮ የመላቀቅ መብቱን የሚጥሱበት ሁኔ ያጋጥማል።

በመሠረቱ የገንዘብ መቀጫ የማስከፈልና የገንዘብ ቅጣትን የማስፈጸም ላፊነት የማረሚያ ቤቶች አይደለም። የገንዘብ መቀጫ የአከፋፈል ሥርዓት ንዴት መከናወን

ንዳለበት በወንጀል ህጉ ከአንቀጽ 94-96 የተቀመጠ ሲሆን ማረሚያ ቤቶች ይህንን ባለመገንዘብ በአመክሮ ሊፈቱ የሚገባቸውን ሰዎች የገንዘብ ቅጣት ስላልከፈላችሁ የአመክሮ ጥያቄ ለፍርድ ቤት አናቀርብ በማለት በመክሮ ሊለቀቁ የሚገባቸውን ሰዎች በህግ ያልተቀመጠ ገደብ የሚፈጥሩበት አንድ አንድ ቦ ም የተፈረደበትን ስር የጨረሰውን ፍርደኛ የተወሰነብህን የገንዘብ ቅጣት ካልተፈጸምክ አንለቅህም ብለው አስረው የሚቆዩበት ሁኔ ያጋጥማል።

ዚህ ላይ አንድ ፍርድ የተቀጣ ሰው የተወሰነበትን የገንዘብ ቅጣት ለመክፈል የሚያስችል የገንዘብ አቅም ያለው ለምሳሌ በማረሚ ቤቱ ያስቀመጠው ገንዘብ ሥራ ሰርቶ የሚያገኘው ገቢ ቢኖረውና ገቢው ለግሉ የሚያጠራቅም ሆኖ ያለ ፍርድ ቤቱ የወሰነበትን የገንዘብ ቅጣት ለመክፍል ፈቃደኛ ካልሆነ የባህሪለውጥ ላለምጣቱና በጥፋቱ ለለመጸጸቱ ንደ አንድ ጠቃሚ መረጃ ተወሰደ የአመክሮ ጥያቄው ውድቅ ሊደረግ ይችላል። ንዲህም ሊሆን አመክሮ የሚያስከለክለው መፈፀም የቻለ ሆን ብለ በማመፅ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ መፈጸም የቻለ ላለመፈጸም ንቢተኛ በመሆኑ በቆየባቸው ጊዜያት በባህሪ ለውጥ በማምጣቱ ላይ ጥርጣሬ የሚያሳድር መሆኑን የሚያመላክትና መክፈል የሚችል ስለመሆኑ ተጨባጭና በቂ መረጃ ሲኖር ነው።

በመሆኑም ከዚህም አንድ ሰው የገንዘብ መቀጫውን ለመክፈል የሚስችለው የገንዘብ አቅም ስሌለውን ና ድሃ በመሆኑ ብቻ በአመክሮ የመልቀቅ መብቱ ሊገደብ አይገባውም።፤ በማናቸውም መንገድ ቢሆን የተፈረደበትን የ ስር ጊዜ የጨረሰ ስረኛ የገንዘብ ቅጣት አልከፈልክም ተብሎ ፍርድ ቤቱ ከወሰነበት የቅጣት ጊዜ በላይ ለአንድ ቀንም ንኳን መዋል የለበትም። በመሆኑም ማረሚያ ቤቶች በዚህ በኩል ያለውን አሰራር ማሻሻልና ህጉን ባገናዘበ መንገድ ቅጣቱን የማስፈጽም ሃላፊነት አለባቸው።

(መ) ማረሚያ ቤቶች በፍርድ ቤቶች የተሰጡትን ውሳኔና ትዕዛዝ የማስፈጸም ላፊነት ያለባቸው ቢሆንም ከዚሁ ጋር የተይይዘ አንድ የተሰጣቸው ስልጣን አለ። ይኸውም በፍርድ የተሰራው ሰው ፍርድ ቤቱ የወሰነበት ሁለት ሶስተኛ የሚሆን ቅጣት በሚፈጽምበት ወቅት ያሳየውን የባህሪ ለውጥ በመከ ተል በአመክሮ ተፈትቶ ቀሪውን ጊዜ በሙከራ መቆየት አለበት ብለው የሚያስቡት ፍርደኛ ፍርድ ቤቱ በአመክሮ ንዲፈ ው ተገቢውን ማስረጃ በማያያዝ ጥያቄ የማቅረብ ስልጣን ሃላፊነት ተሰጥቷዋል።

ማረሚያ ቤቶች አንድ አስረኛ በአመክሮ ንዲፈ ጥያቄ የሚያቀርቡት ተከሳሽ በወንጀል ህግ አንቀጽ 202 የተደነገጉትን ሁኔ ዎች ሲያሟላ መሆን ንዳለበት ህጉ በግልጽ የሚያስቀምጥ ቢሆንም ማረሚያ ቤቶች ይህንን ለመብት የሚስችሉ መስፈርቶቸች

ሳይወጡ ጥቂት ማረሚያ ቤቶች ጥያቄ ለማቅረብ ፈቃደኛ የማይሆኑ ሲሆን ለአንዳዶቹ ደግሞ ጥያቄውን የሚያቀርቡበት ሁኔ ለመኖሩና በዚህም ስልጣንን አላግባብ አብዛኛ ዎቹ ደግሞ ለሁሉም ስረኞች አመክሮ ንደመብት በመውሰድ ጥያቄ የሚያቀርቡ በመሆናቸው በዚህ በኩል የወንጀል ህጉ የጣለባቸውን ሃላፊነት ካለመረዳት የመጣ ሊሆን ስለሚችል አሰራራቸውን ማስተካለልና ህጉን የማስፈጸም ግዴ አለባቸው።

5.3.2 ሌሎች አካላት ህግ አለማክበር

በማረሚያ ቤቶች ላይ የሚፈጥርባቸው ችግር ማረሚያ ቤቶች አንድ አንድ መሰረ ዊ ህጎች ባለመከተላቸው የሚፈጠረው ችግር ንዳለ ሆኖ የሌሎች አካላት አደረጃጀት ባለመሟላቱ ምክንያት የፍትህ አካላት የበኩላቸውን ላፊነት በህግ አግባብ ባለመወጣ ቸው በማረሚያ ቤቶች ላይ የሚፈጠሩ ችግሮች አሉ።

ማረሚያ ቤቶች በባህሪያቸው የወንጀል ክስ ቀርቦባቸው በተለያየ ምክንያት በተለይም በ ስር ሆኖ መከፈላቸው በህግ ወይም በፍርድ ቤት የተወሰነባቸው ተከሳሾችና በፍርድ የተቀጡ ሰዎች የሚስተናግዱ ተቋማት በመሆኑም በ ኛ አገር ፖሊስ ምርመራ በሚያደርግበት ጊዜ ተጠርጣሪዎ የሚቆዩበት ማረሚያ ቤት የሌለ በመሆኑ የጊዜ ቀጠሮ ስረኞች ያስተናግዳሉ ። በመሆኑም የ ኛ አገር ማረሚያ ቤቶች በሌሎች አገሮች ማረሚያ ቤቶች ና ማረሚያ ቤቶች የሚሰጡት አገልግሎት ቀላቅለው ለመስጠት በሚምክሩበት ወቅት ፣አድካሚና ፣መሠረ ዊ ተልዕኳቸው ላይ ማለትም ጥፋተኞችን በማረ ም.. መልካም ዜጋ በማድረግ ጉዳይ ከማተኮር ይልቅ ፣በጥበቃ ሥራና ተተርጣሪዎችን ለጊዜ ቀጠሮ በማመላለስ ፣ ንዲጠመዱ ያደርጋቸዋል።

- ይህ ንዳለ ሆኖ፣ማረሚያ ቤቶች በጊዜ ቀጠሮ ለተወሰነ ቀናት ንድቆይ ያተሳካላቸው ተጠርጣሪ ከተቀበሉ ጊዜ ቀጠሮ የጠየቀበት ፖሊስም ሆነ፣ በጊዜ ቀጠሮ ንዲቆይ ት ዛዝ የሰጠው ፍ/ቤት ተለዋጭ ት ዛዝ ሣይሰጡ የውሃ ሽ ሆነው የሚቀሩበት ጊዜ ፣ተጠርጣሪውን ንዳይፈቱት ፣የተጠረጠረበት ወንጀል ከባድ ፣ መሆንና መላቀቁ ፣በህዝብ ድህንነት ላይ የሚፈጥረውን ስጋት በማሰብ ተጠርጣሪዎች ንዳይቆዩት ደግሞ፣ በተጠርጣሪው በማረሚያ ቤት ንደሚቆይ በዳኛ የተወሰነው የጊዜ መጠን ፣ያለቀ በመሆኑና ስሩ ሕግወጥ ፣ስለሚሆንባቸው ፣በሁለት ጫፍ የሚወጠሩበት ሁኔ ያጋጥማል። በመሆኑም የዚህን አይነት ችግር ለመፍ ት ፣የመረጃ ፍስት ሥርዓቱን በፍትህ አካላት ፣ መሀከል ቃልጠፋ ንዲሆን በማድረግ የጋራ መፍትሄ መስጠት ካልተቻለ ፣

የማረሚያ ቤቶች ሥራ ፣ ላይ ና በተጠርጣሪው መብት ላይ ፣የሚያሳድረው ተፅዕኖ በቀላሉ የሚ ይ መሆን ፣ ያለበትም።

- ፍርድ ቤቶች የ ስራት ወይም የጽኑ ስራት ቅጣት ሲወስኑ ፣ ቅጣቱ ፣ ከመቼ ጀምሮ መቆጠር ንዳለበት በተለይም ተከሳሽ በጊዜ ቀጠሮ የቆየበት ጊዜ አብሮ የሚ ሰብለት ስለመሆኑ ፣ወይም አለመሆኑ ፣ት ዛዝ መስጠት ንዳለባቸው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 115 የሚደነገግ ቢሆንም ፍርድ ቤቶች ተከሳሽ በጊዜ ቀጠሮ ስለቆየበት ጊዜ ምንም አይነት ውሳኔ ሳይሰጡ በአንድ ዓመት ስራት በአስር ዓመት ፅኑ ስራት ቀጥተነዋል የሚል ፍርድ የሚሰጡበት አጋጣሚ መሆኖሩንና ይኸውም ቅጣቱን በማስፈጸም ሂደትና በቅጣት ጊዜው አቆጣጠር ምክንያት በፍርድ በ ሰረው ሰውና በማረሚያ ቤቱ መካከል ፣አለመግባባት የሚፈጠርት በመሆኑ ፣ ማረሚያ ቤቶች ንዲህ አይነት ግልጽ ያልሆነ ፣ ት ዛዝ ሲደርሳቸው የ ስረኛው መለቀቂያ በደረሰና ችግሩ በተከሰተ ጊዜ ሳይሆን ፣ወዲያውኑ ፍርደ ቤቱ ስለ ቅጣት አፈጻጸምና የ ሰረው ሰው በጊዜ ቀጠሮ በ ስር የቆየበት ጊዜ ከቅጣቱ ጋር የሚ ሰብለት ንደሆነ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 115 መሠረት ግልጽ መልስ ንዲሰጥ በመጠየቅ ፣ፍርድ ቤቱ የሚሰጠውን ማብራሪያ በፍርድ ከተቀጠው ሰው ማህደር ጋር ማያያዝ ማስፈጸም ይጠበቅባቸዋል።
- ማረሚያ ቤቶች በበርካ ወንጀሎች በተለያየ የተከሰሱና ፍርድ የተሰጣቸው ሰዎች ያጋጥሟቸዋል። አንድ በፍርድ የተቀጣ ሰው ፣ በማረሚያ ቤት ፣ ፍርዱን በመፈጸም ላይ ንዳለ ፣በተከሰሰበት በሌላ ወንጀል ፣ጥፋተኛ ሲባል ፣ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ በሌላ ወንጀል የተቀጣ መሆኑን አውቆ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 186 መሠረት ንዲወሰን ፣ ማመልከትና ማስወሰን ሲገባቸው ፣ይህንን ሳያደርግ አንድ ሰው አንድ ወንጀል 10 ዓመት ፣በሌላው ወንጀል 15 ዓመት ደግሞ በሌላ ወንጀል 10 ዓመት ጽኑ ስራት ንዲቀጣ ፍርድ ተሰጥቶበት ፍርዱንም ማረሚያቤቶች ንደያስፈጽሙ ት ዛዝ ይመጣላቸዋል። ነዚህ ሶስት ፍርዶች የተሰጠው ቅጣት ሲደመር 35 ዓመት ጽኑ ስራት ቅጣት የሚመጣ ሲሆን ይኸውም በወንጀል ሕጉ ፣አንቀጽ 108 ከተቀመጠው 25 ዓመት ጣሪያ ፣የሚበልጥ ሆኖ ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪ ማረሚያ ቤቱ ፣ቅጣቱን ንዴት ማስፈጸም ንዳለበት ግራ ይጋባል። ይኸውም ማለት ፍርድ ቤት ፍርድ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ ነው የሌሉንም ቅጣት ቀን የሚቆጥረው ውይስ በመጀመሪያ አንደኛውን ከዚያ ሁለተኛውን ፍርድ ነው የሚያስፈጸመው የሚለው ውዝግብ ያስነሳል። የዚህ አይነት ሁኔ ሲያጋጥማቸው ጉዳዩ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 186

ይቶ ልባት ንዲሰጠው የሚመለከተውን የዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤትና ፍርድ ቤት ማረሚያ ቤቶች ካልጠየቁ ፣ጉዳዩ ፣ በፍርድ የተሰራውን ሰው መብት ጅግ በጣም የሚጎዳ በመሆኑ ፣ በዚህ የአሠራር ክፍተት የተፈጠረውን ችግር ንዲፈ ፣ማረሚያ ቤቶች ጥረት የማድረግ ፣ ላፊነትና ግዴ አለባቸው።

5.4 <u>የማረሚያ ቤቶች ሀላፊዎችና ሰራተኞች የ ስረኞችን መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴ</u> አለመጣት

ከፍርድ በጥበቃ ሥር ያሉ ሰዎችን መብት የማክበር ግዴ ከላይ ንደተገለጸው በጥበቃ ሥር ያሉና በፍርድ የ ሰሩ ፣ሰዎች ማረሚያ ቤት ሆነው ሊያከብሩላቸው የሚገባ፣መብቶች አሏቸው ። ነዚህ መብቶች በቂ የምግብ ፣የመኝ የህክምና ግልጋሎት ፣በማግኘት ብቻ የተወሰኑ አይደሉም ከዚህ በተጨማሪ ፣ ራሚዎች

- ከዘር ከሃይማኖት በማህበራዊ አቃቅ አድሎና ልዩነት የመጣበት መብት
- ኢሰብዓዊ ከሆነ ፣ቅጣት ወይም አያያዝ ፣የመጠበቅ መብት
- የሞት ፍርድ በአግባቡ ተፈጻሚ ካልሆነ በስተቀር በህይወት የመኖር

-በዘመዶቻቸው የመጎብኘት ና በደብዳቤና በሌሎ መንገዶች ግንኙነት የመፍጠር መብት

- ስለ ንብረቱ ፣ኑዛዜ ማድረግ ፣
- ከአንዱ ማረሚያ ቤት ወደ ሌላ ማረሚያ ቤት የመዛወር መብት ፣
- የያዘውን ገንዘብ በአደራ የማስቀመጥ ፣መብት ፣
- በጥበቃና በፍርድ የ ሰሩ ሰዎች ገቢ የሚያስገኝለት ሥራ የማምረት መብት
- መረጃ የማግኘት መብት
- በጥበቃ ሥር ያሉት በፍርድ የተከሰሱ ሰዎች ገቢ በሚያስገኛ ማህበር የመደራጀት መብት ፣
- አቤቱ የማቅረብና ለአቤቱ ው ምላሽ የማግኘት መብት ፣
- የ ምነትና የሃይማት ነጻነት ፣
- የዲስፒሊን ክስ ፣የማተባበልና የመከላከል መብት
- ሲለቅ ወደ ቤተሰቦቹ የሚመለስበት ስንቅ ና የትራንስፖርት ገንዘብ የማግኘት መብት ንዳለው በዓለም አቀፋዊ ስረኞች አያያዝ መመሪያና በአገራችንም የአንድ አንድ ክልሎች ከወጡ የታራሚዎች አያይዝና መወሰኛ ደንብ፣ለመረዳት ይቻላል። ዚህ ላይ ማረሚያ ቤቶች ራሚዎችን የማረምና ደህንነ ቸውን ለማረጋግጥ የሚያስችል

ጥበቃ፣ለመስጠት ያመቻቸውን ዞን ፣በጥበቃና በፍርድ የ ሰሩ ሰዎችን ወጣት ጥፋተኞችን ፣ከአዋቂዎች ፣ሴት ስረኞች ፣ከወንዶች በቀላል ስራት የተቀመጡትን በጽኑ ስራት ከተቀጡት ፣በሞት ፍርድ የተቀጡትን ከሌሎ ስረኞች በቀጠሮ ላይ ያሉትን ከተፈረደባቸው ንደዚሁም የተፈረደባቸውን ንደ ፍርደቸው ክብደት ቅጣቱን ለመፈጸም ከሚቀራቸው ጊዜ አኳያ በመመደብ ፣ የጥበቃና የማረም አገልግሎት ንዲሰጡ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሆኑም የተለያዩ መደብ ውስጥ የተፈረጁ ስረኖች የሚያደርጉ ጥበቃ ና የተሀድሶ የተለያየ የመሆኑ ሁኔ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ከዚህ አንጻር ስናየው ስረኞች (ካ ጎራዝ) ማድረግ አንድን ስረኛ ጸ ውን ፣ዘሩን የፖሊቲካ አስተሳሰቡን ማህበራዊ አቅሙን ፣ አይማኖቱን ና መሳሰሉትን ዓላዊ የሆኑ ፣ነገሮች መነሻ በማድረግ ልዩነትና አድሎ ከመፈጸም ጅግ በጣም የተለያየ ነው፡፡ ማረሚያ ቤቶች ስረኞችን ፣በሕግ በተቀመጠው መንገድ የተጠናከረ ወይም ልል የሆነ የጥበቃና የክትትል ሥራ ፣ የማከናወን ተለያዩ የተሀድሶና የምክር አገልግሎት የመስጠት መብት ቢኖራቸውም ፣ ከላይ የተነሱትን ነገሮች መነሻ በማድረግ ድሎች ልዩነት ከመፈጸም መ ቀብ አለባቸው፡፡

- ከሁለተኛ ደረጃ በጥበቃና ከፍርድ የ ሰሩ ሰዎች ከማናቸውም ኢሰብአዊ ና ጭካኔ ከምላበት አያያዝ ፣የመጠበቅ ሕግ መንግሥ ዊ መብት አላቸው፡፡ በጥበቃ ሥር ያና በፍርድ የ ሰሩ ሰዎች በማረሚያ ቤት ፣ ያሉ ከባድ ወይም ቀላል የዲስፒሊን ጥፋት አጥፍተው ከሆኑ ፣ጉዳያቸው በዲስፒሊን ኮሚቴ መ የትና በዚያው መሠረት ፣የዲስፒሊን ርምጃ ለወሰደባቸው ይገባል ንጂ ፣ ስረኞችን አላግባብ መደብደብ ፣የአካል ጉዳት ማድረስና የመሳሰሉትን ተግባራት መፈጸም የለባቸውም

ከዚህ ጋር አብሮ የሚነሳው በጥበቃና በ ጀባ ወቅት የ ስረኞችን ንቅስቃሴ የሚገድለቡ ንደ ካቴና ና ሰንሰለት የመጠቀምና ወይም ሀይል የመጠቀም አስፈላጊነት ነው፡፡ ማረሚያ ቤቶች የማህበረሰቡን ድህንነት ከማስከበርና የፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ለማስፈጸም የሚያከናውኑት ተግባር አንጻር አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሀይል መጠቀምን ፣የሚጠይቅ ወይም ንቅስቃሴ በሚገድብ መሳሪያዎች ለጊዜው መጠቀምን የሚጠይቅበት ጊዜ መኖሩ አያከራክርም፡፡ ከዚህ በመነሳት ማረሚያቤቶች ተመጣጣኝ በሆነ መንገድ ሀይል ና ንቀስቃሴ የሚገድቡ መሳሪያዎችን ንዲጠቀሙ ለማደረግ ስለ ሀይል አጠቃቀም አስፈላጊነትና የሀይል አጠቃቀም ሥርዓት ንዲሁም ንቅስቃሴ የሚገድቡ መሳሪያዎች አጠቃቀም ሥርዓት ዝርዝር የሆነ ደንብና መመሪያ ማውጣት በዚያ መሠረት መመራት ይገባል፡፡

ዚህ ላይ ሳያነሳ መ ለፍ የሌለበት የማረሚያ ቤት ሠራተኖች ሕግና ሥርዓትን ለማስከበር ሳይሆን በግል ፍላጎትና ስሜ ቸው በመነሳት በ ስረኞች ላይ የሚወስዱት

የሀይል ርምጃ ለሚያደርሱት ጉዳት ሙሉ በሙሉ በወንጀል ላፊና ተጠያቂ ንደሚሆኑ ሲሆን በሥራ ሂደ ቸውን ሁኔ ው ከሚፈልገውና በሚፈቅደው ፣መጠን በላይ ሀይል ከተጠቀሙ ተጠያቂ የሚሆኑበት ሁኔ መኖሩን ነው።

- በጥበቃና በፍርድ የ ሰሩ ሰዎች ከዘመዶቻቸው ከጠበቆቻቸው ጋር በሚገናኙበት ጊዜ የጥበቃ መከናወን አለበት። የሚቀበሏቸው ቃዎች ና ማናቸውም ወረቀት ፣መፈተሽ በማረሚያ ቤቱ በኩል ይቶ ንዲወጣ ማድረግ የሕብረተሰቡን የሌሎች ራሚዎችን ደህንነት ለማስከበር አስፈላጊ ናቸው። በመሆኑም ፣የግኙነት ሥርዓቱን <u>የሚገናኙበት</u> ዘንድ የሚደረገው ጥበቃ ና የጠባቂው መብትና ግዴ በዝርዝር በማስቀመጥ በአንድ በኩል የ ስረኞች ከዘመዶቻቸው ጋር የመገናኘት መብት በሌላ በኩል ደግሞ የማረሚያ ቤቱ ቁጥጥርና ክትትል የማድረግ ላፊነት ሚዛናዊ በሆነ ሁኔ ንዲፈጸሙ ማደረረግ ይገባል።
- በጥበቃና በፍርድ የ ሰሩ ሰዎች ከመ ሰራቸው በፊት ስለነበራቸው ንብረት ኑዛዜ ወይም ስጦ ለማድረግ ቢፈልጉ ይህንኑ ለማድረግ ንዲችሉ ከውልና ማስረጃ የሥራ ላፊነዎች ጋር የመገናኘት ችሎ ያላቸው ምስክሮች የማቅረብና ኑዛዜው ለሚመለከተው ክፍል የማስተላለፍ ማረሚያ ቤቶች አለባቸው። ከዚህ አንጻር ማረሚያቤቶች የ ሰሩ ሰዎች የማፈጽሟቸውን ተግባራት የመደገፍቀ ላፊነት አለባቸው። የይግባኝ መብቱን የጨረሰ በፍርድ የተቀጣ ፍርደኛ ቤተሰቦቹና ዘመዶቹ ወዳሉበት ማረሚያ ቤት ተዛውሮ ቅጣቱን የመፈጸም መብት አለው። ይኸውም በሚሆን ጊዜ ማረሚያቤቶች የፍርደኛውን የዝውውር ጥያቄ በአግባቡ ማስተናገድና ምላሽ መስጠት የሚገባቸው ሲሆን አንድ አንድ ማረሚያቤቶች የአጃቢዎችን የትራንስፖርትና የውሎ አበል መክፈል ካልቻልክ ከአንዱ ማረሚያ ቤት ወደ ሌላው ማረሚያ ቤት የማዛወር ሂደቱን ንዲፈጽምም ሲሉና ድሀ የሆኑ ሰዎችን ለቤተሰቦቻቸው ቀርበት ባለቤት አካባቢ ቅጣ ቸውን የመፈጸም መብት ሲያሳጡ ይ ያሉ። ይኸውም ጥንቃቄ የሚጠይቅና መስተካክል ያለበት ተግባር ነው።
- ራሚዎች ገቢ የሚያስኝ ማህበር ለምሳሌ በህብረት ሥራ ማህበር የመደረጃት መብት ያላቸው ሲሆን ዚህ ላይ ማረሚያ ቤቱ የማህበሩ አባላትና የማህበሩ አመራር ግንኙነት ግልጽና በመርህ ላይ የተመሰረተ ንዲሆን ማድረግ የማህበሩ ንብረት ንዳይባክን ስረኞች የቁጥጥር ፣የክትትል የሚያደርጉበትን ምቹ ሁኔ መፍጠር አለባቸው። ንዲሁም ስረኞች በግላቸው ገቢ የሚያስገኝ ሥራ ላይ ንዲሰማሩ ጥረት መደረግ አለበት።
- ማረሚያ ቤት ሰዎች ስብስብ ብለው የሚኖሩበት ቦ ነው። በመሆኑም በተለያየ መንገድ በአቤቱ ና ቅሬ መነሻ የሚሆኑ ሁኔ ዎች ይፈጠራሉ። ነዚህም

- የማረሚያ ቤት ሠራተኞች በሥራቸው ምክንያት ከ ስረኞች ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ፣
- የማረሚያ ቤት ሠራተኞች በግል ከ ስረኞች ጋር በሚፈጥሩት ግንኙነት
- ስረኞች መካከል በሚኖር የ ርስ በርስ ግንኙነት
- ስረኞች ና በህብረት ሥራ ማህበር መሪዎች ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት
- የማረሚያ ቤቱ ሠራተኖች በሥራቸው ምክንያት ባላቸው ግንኙነት መብ ችን ተጥሶብናል የሚሉ የተለያዩ አቤቱ የሚያቀርቡ በፍርድ የ ሰሩ ና በጥበቃ ሥር ያሉ ሰዎች ያጋጥማል፡፡ በዚህ ጊዜ መርህንና ሕግና ሥርዓትን ተከትሎ አቤቱ ቸውን ተጣርቶ ምላሽ የማግኘት መብት አላቸው የማረሚያ ቤት ላፊነዎችና ሠራተኞች የ ስረኞች አቤቱ የመቀጠል ምላሽ የመስጠት ላፊነት ንዳለባቸው ተረድተው በዚህ በኩል የሚ ዩ ችግሮችን መቅረፍ አለባቸው፡፡ ከዚህ በተጨመሪ የሌሎችን ስረኞች መብት በማይነካ ሁኔ በፍርድና በጥበቃ ሥር ያሉ ሰዎች የዕምነት ነጻነት ማክበር አስላጊ የሆኑ ሃይማኖ ዊ መጽሐፎች በተለያየ መንገድ በማሰባሰብ የማቅረብ ግዴ ማረሚያቤቶች አለባቸው፡፡
- ማረሚያቤቶች ውስጥ ያሉ ጥበቃ ሥር ያሉ ወይም በፍርድ የ ሰሩ ሰዎች በማረሚያ ቤቱ ሠራተኞች ፣በማረሚያ ቤቱ ንብረት የጸጥ ሥራ ወይም በሌሎች ስረኞች የአካል ደህንነት ፣ንብረት ና መብት ላይ የዲስፒሊን ጥፋት የሚፈጽሙበት ሁኔ ያጋጥሟል፡ ፡ ንደዚህ ሲሆን ማረሚያ ቤቱ የዲስፒሊን ክሱ ሲሰማ ስረኛው መልስ የመስጠት መብት ማክበርና የመከላከያ ማስረጃውን የማሰማት መብቱን ማክበር ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም አንድ በፍርድ የ ሰረ ሰው የ ስር ጊዜውን ሲጨርስ ወደቤተሰቦቹ የሚሄድበት የትራንስፖርት ገንዘብና ስንቅ የሚችገርበት ሁኔ ያጋጥማል፡፡ ንዲዘህ በሆነ ጊዜ ማረሚያቤቶች ሰውየው ወደ ቤተሰቦቹ የሚሄድበት ትራንስፖርትና ስንቅ የሚሆነው ገንዘብ ድጋድ ካላደረገ አጠቃላይ በማረሚያ ቤቱና በመንግሥት ገጽ ላይ አሉ ዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር በመሆኑ ይህንን ድጋፍ የማድረግ ይገባዋል፡፡

ከላይ ከተገለጹት በተጨማሪም ሴት ስረኞች በሴትነ ቸው ምክንያት በ ርግዝና ፣ በወሊድ ና በመሳሰሉት የሚያስፈልጋቸውን ልዮ የመኝ ና የምግብ አቅርቦት ከግምት ውስጥ ያስገባ ፣ ንክብካቤ የማድረግ ግዴ በማረሚያ ቤት ሠራተኞች አለባቸው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተገለፁት በፍርድ አፈፃፀም ሒደት የሚታዩ ችግሮች የወንጀል የፍትህ ሥርዓቱ ግቡን እንዳያሣካ ትልቅ እንቅፋት የሚፈጥሩ በመሆኑ በትኩረት መታየትና መሻተካከል አለባቸው፡፡

ማጠቃለያ

የአገሪቱ እና የክልል የወንጀል የፍትህ ሥርዓቶች የተጣለባቸውን ተልዕኮ በአግባቡ ለመወጣት እና የወንጀል ህጉን መሠረታዊ ግብ ለማሣካት መሟላት ያለባቸው የህግ ማዕቀፍ የአሠራር ሙዋሉች ጠቋሚ መመሪያዎች በማሟላት ህጉን ለመፈፀም አስፈላጊ የሆኑ አደረጃጀቶች ተፈጥሮ ሥራቸውን እንዲሠሩ ማድረግና ህግን በመተርጎምና በማስፈፀም ሒደት ያሉትን የግንዛቤ የክህሎትና የሥነ ምግባር እጥረቶች በየወቅቱ እያጠኑ የሚፈቱበት መንገድ ማፈላለግ ስለሚያስፈልግ ሁላችንም ሥርዓቱን ወጤታማ ለማድረግ የበኩላችንን ጥረት ማድረግ ይገባናል ፡፡

ዋቢ መፅሐፍና ማጣቀሻ ፁሑፎች

1. Amnesty International : Fair Trial Manaual, Amnesty International
Publication 1998

2. Baccaria's Argument an Grimes and Punishment, Crime theory
Com

3. Stanford Encyclopedia of Philosophy, Legal Punishment and its
Justification

4. Gerhard, Muller and Laufer, Criminal Justice, mcoraw will 1994

5. Stalt Z burg and Capra ,
American Criminal Procedure, cases and commentary,
Fifth Edition 1996

6. ICRC Community Service as an Alternative to imprisonment
2004

7. Stenu, Alternatives to prison in developing countries,
International Center for prison studies, 1999.

8. Robert Artnur Melin, Evidence in Ethiopia, HsIU, 1972 Vol.1,
Vol.2 and Vol.3

9. FDRE Comprehensive Justice system Reform Program. Baseline study Report.

Ministry of capacity Building, 2005

10. የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ

11. የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ

12. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት

13. የልዩ ልዩ ተቋማት ሪፖርቶችና በፍርድ ውሣኔ ያገኙ ጉዳዬች ፣

ማውጫ

ገጽ

መግቢያ **1**

ምዕራፍ አንድ ወንጀል ሚካላከል በጠቅላላው

1.1 የወንጀል ሚካላከል ደረጃዎች 3

1.2 የመጀመሪያ ደረጃ የወንጀል ሚካላከል ተግባራት 7

1.3 ሁለተኛ ደረጃ የወንጀል ሚካላከል ተግባራት 8

ምዕራፍ ሁለት የወንጀል ምርመራና የሚከረጃ አሰባሰብ ሒደት

2.1 ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ ስላሉት ሒደቶች በጠቅላላው 10

2.2 የወንጀል ምርመራ ትርጉምና ጠቀሜታ 14

2.3 ወንጀል ምርመራ ከመጀመሩ በፊት ሊመረመሩ ስለሚገባቸው ጉዳዬች 18

2.4 መረጃንና ማስረጃን ስለማሰባሰብ 20

ምዕራፍ ሶስት ስለ ማጣራት የወንጀል ክስ አቀራረብና የመጣት ሒደት

3.1 ስለ ማጣራት ሂደት በጠቅላላው 24

3.2 የክስ አቀራረብ ሒደትና ችግሮቹ 25

3.3 የመጣት ሒደትና ችግሮቹ 27

ምዕራፍ አራት የወንጀል ፍርድ አሰጣጥና ቅጣት አወሳሰን

4.1 ስለ ወንጀል ፍርድ አሰጣጥ 29

4.2 የወንጀል ቅጣት አወሳሰን 31

ምዕራፍ አምስት የወንጀል ፍርድ አፈፃፀምና ችግሮች

5.1 ስለ ማረሚያ ቤቶች ሀላፊነትና ግዴታ በጠቅላላው 36

5.2 የማረሚያ ቤት ተልዕኮ 38

5.3 ማረሚያ ቤት ተልዕኳቸውን በማስፈፀም ሒደት የሚያጋጥሟቸው ችግሮች 40

5.3.1 ህጉን ባለመረዳት የሚፈጠሩ ችግሮች 41

5.3.2 ሌሎች አካላት ህግ ባለማክበራቸው የሚፈጠር ችግር 45

5.4 የማረሚያ ቤት ሀላፊዎችና ሠራተኞች ግዴታ 47

ማጠቃለያ 51

የወንጀል የፍትህ ሥርዓት መሠረታዊ ግብ፣ በአሠራር ላይ የሚታዩ ክፍተቶች ችግሮችና የመፍትሔ አቅጣጫዎች

ከታህሣሥ 4 ቀን 2000 – ታህሣሥ 7 ቀን 2000 ላዘጋጀው የአቅም ግንባታ ሴሚናር የቀረበ

በዓሊ ሙሐመድ ዓሊ

ታህሣሥ /2000 ዓ.ም
አ ዋ ሳ